# ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ


## የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ
## የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል


# "አስራ ሁለቱ እንግዶች" ተውኔት ከሞራላዊ እና ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ትንተና


**በ**

**ሃይለየሱስ ሰውነት**


**2017 ዓ.ም**

# ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

## የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ
## የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

## "አስራ ሁለቱ እንግዶች" ተውኔት ከሞራል እና ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ትንተና

**በ**

**ሃይለየሱስ ሰውነት**

**የጥናቱ አማካሪ**

**መምህርት ሜሮን ተስፋዬ**

**በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለባችለር ኦፍ አርትስ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ**

**2017 ዓ.ም**

የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪው ስም____________________

ፊርማ_________________________

ቀን__________________________

ይህ ጥናት በሃይለየሱስ ሰውነት "አስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት ከሞራል እና ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ትንተና"በሚል ርዕስ የሰራዉን የመጀመሪያ ድግሪ ሚሟያ ፅሁፍ የዩኒቨርስቲውን ጥራት እና ደረጃ ያሟላ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት መሆኑን ማረጋገጫ ነው።

ይህም በፈታኝ ኮሚቴ ተረጋግጧል።

ፈታኝ አንድ

ስም____________________

ፊርማ__________________

ቀን___________________

ፈታኝ ሁለት

ስም____________________

ፊርማ___________________

ቀን_______________________

## ምስጋና

በመጀመሪያ አስጀምሮ ለአስጨረሰኝ ለልዑል እግዚአብሔር እስከ እናቱ ድንግል ማሪያም ክብርና ምስጋና ይሁን። ከፈጣሪ በታች ለእናቴ ወ/ሮ ዙማም አለሙ እና ለአባቴ አቶ ሰውነት ተፈራ ላቅ ያለው ምስጋና ይድረስልኝ እያልኩ በመቀጠል ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ ሳዘጋጅ ከጎኔ በመሆን ሀሳብና አስተያየቷን ሳትነፍግ ላማከረችኝ መምህርት ሜሮን ተስፋዬ ምስጋናዬ ይድረስልኝ።

# አበርክቶ

ተፈጥሮ እዳ ነው! ለምን ካልሽኝ እናቴ ነሽ!…የእናትነትሽን እዳ እይልኝ እስኪ… እድሜሽን በሙሉ ለእኔ እንጅ ለአንቺ አላሰብሽም እኮ….. ግላጭ  ግብር የሌለው ፍቅርን ተሸክመሽ ሰው ላደረግሽኝ ውዷ እናቴ ወ/ሮ ዙማም አለሙ አበርክቶዬ ይሁን ላ'ንቺ!!!

# አጠቃሎ

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አስራ ሁለቱ እንግዶች ትርጉም ተውኔት ከሞራላዊና ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ተተንትኗል። ተውኔቱ ትልቅ አስተዋፅ ያላቸውን ፅንሰ ሀሳቦች፤ ፍልስፍናዎች፤ ትችቶችን ይዞ በትርጉም ዘርፍ አለምን የዞረ ተውኔት ነው። አጥኚውም ይህንን ተውኔት ገላጭ የምርምር ዘዴ በመጠቀም በሁለቱ የሂስ ነድፈ ሀሳቦች ማለትም ከሞራላዊ ሂስ አንፃር በመተንተን የተለያዩ በተውኔቱ የተንፀባረቁ ሞራላዊ እሳቤዎችን፤ ከሞራል አንፃር የገፀባህሪያትን ትንተና ከደካማና ከጠንካራ ጎኖች ጋር ቀረቧል። እንዲሁም ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር የሚነሱ ጥያቄያዊ ምርርመራዎችን በተውኔቱ ላይ በመተንተን ጥናታዊ ፅሁፉን አዘጋጅቷል። በጥናታዊ ፅሁፉም የተውኔቱ ደካማና ጠንካራ ጎኖች በፅንሰ ሀሳቡ ላይ በመመርኮዝ ተተንትኗል። አስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት በታሪኩ ውስጥ ይዞት ከተነሳው ጭብጥ ብሎም የተለያዩ ጥቃቅን አመለካከቶችና የንድፈ ሀሳቦች ምልከታ በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጥሩ ጎኑ አመዝኖ ይገኛል።

ምዕራፍ አንድ .......... 1
1.መግቢያ .......... 1
1.1 የጥናቱ ዳራ .......... 2
1.2 የጥናቱ አላማ .......... 2
1.2.1 የጥናቱ አብይ አላማ .......... 2
1.2.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ .......... 2
1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ .......... 2
1.4 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች .......... 2
1.5 የጥናቱ ወሰን .......... 3
1.6 የጥናቱ ዘዴ .......... 3
1.7 የጥናቱ አደረጃጀት .......... 3
1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች .......... 4
ምዕራፍ ሁለት .......... 5
2. የንድፈ ሀሳብ ቅኝት .......... 5
2.1 ተውኔት .......... 5
2.2 ሂስ .......... 5
2.3 የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ .......... 6
2.4. ሞራላዊ ሂስ .......... 8
2.5 የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት .......... 9
ምዕራፍ ሶስት .......... 11
3. የመረጃ ትንተና .......... 11
3.1 የአስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት ታሪክ .......... 11
3.2 አስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር .......... 11
3.2.1 የገፀ-ባህሪያት አሳሳል ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር .......... 11
3.2.2 የስርዓቶች ወይም ተቋማዊ የዘረኝነት ምርመራ .......... 13
3.2.3 የተለያዩ ውክልናዎች .......... 13
3.2.4 የተከሳሹ አመለካከት .......... 13
3.2.5 ተውኔቱ ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ለማህበረሰቡ ያለው ጠቀሜታ .......... 13
3.3 አስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት ከሞራላዊ ሂስ አንፃር .......... 14
3.3.1 በተውኔቱ ውስጥ ያሉት ገፀባሕርያት በሞራላዊነት እንዴት ተስለዋል? .......... 14
3.3.2 ተውኔቱ የተለያዩ ሞራላዊ ዕሳቤዎችን ያነሳል? .......... 18
ሀ. ሞራላዊ አንፃራዊነት .......... 18
ለ. የበጎነት ሞራል (የባህሪ እና የሞራል ታማኝነት) .......... 19
*ሐ. ነፃ ፍቃድ* .......... 19
3.3.3 የስርዓት ኢፍትሀዊነት .......... 19
3.3.4 የፍትህና የምህረት ክርክር .......... 19
*3.3.5 የግለሰብ ሞራላዊ ጀግንነት* .......... 20
ምዕራፍ አራት .......... 21
4. ማጠቃለያ .......... 21
ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው .......... 23
ዋቢ መፅሀፍት .......... 25

## ምዕራፍ አንድ

## 1.መግቢያ

ጥበብ ዘውጓን እየቀያየረች የፈጣሪዋንም የታዳሚዋንም ቀልብ አንድ ታደርጋለች። አድማጩ፤ አንባቢው፤ ታዳሚው ሁሉም በጥበብ አውድ በኩል አልፎ ሰዋዊ ስሜቱን፤ ተፈጥሯዊ መገለጡን የሚያገኝበት፤ ጥበበኛውም የውስጠቱንና የነፍሱን መሻት የሚያወጣበት መድረክ ኪነጥበብ ነው። የጥበብ ሰዎች እንደ ንዕረተ አለማቸው ( world view ) እንደ አደጉበት ባህል፤ እንደ ታሪኮቻቸው፤ እንደ ፖለቲካ አስተሳሰባቸው፤ እንደሚከተሉት ሀይማኖት፤ ውስጣቸው እንደሚብሰለሰለው የፍልስፍና እሳቤዎቻቸው በተለያዩ የኪነጥበብ መስኮች ስራቸውን ያቀርባሉ። ጥበብ በመለኮታዊ ሀይሏ፤ ከነባራዊው በሚነጥለው ንዕረተ-አለሟ ለጥበበኛው ድፍረትን ታጎናፅፋለች።

የኪነጥበብ ስራዎችን ከስር ከስር እየተከተሉ ከጥበባዊ ፋይዳቸው አንፃር በፅንሰ ሀሳቦችና በየራሳቸው ህግጋት መሰረት ሂስ የሚሰጡ ሃያሲዎች ለጥበብ ዘላቂ ህልውና ጉልህ ሚና አላቸው። ነገርግን የኋላ ታሪካችን ተመልሰን ስናየው በኪነጥበብ ስራዎች ላይ ሂስ ( በወቅቱ ስሙ "ሳንሱር" ) የሚሰጠው ወይም ጥበብ ጥበብነቷ የሚለካው በጥበብነቷ ሳይሆን በአገዛዙ ስርዓት ላይ በምታመጣው ተፅዕኖ እንደነበር ታሪክ ምስክር ነው። ዛሬስ?..ለዛ ነው ባህር ማዶ ተሻግረን በባዕድ ሀገራት የኪነጥበብ ነፃነት እንቀና ዘንድ የተገደድነው።

ሬግናልድ ሮስ በ1920 ( እ.አ.አ ) በኒዎርክ ከተማ የተወለደ ደራሲ ነው። በየፊልም ድርሰቶቹ በሚያነሳቸው ሀሳቦች ትልቅ ዝናን አትርፎ የነበረ ደራሲ ነው። ከስራዎቹ መካከል በደምብ ከአለም ጋር ያስተዋወቀው “12 አንግሪ ማን” የተሰኘው ፊልም በ1954 ለእይታ ሲያቀርብ አንቱታን አግኝቶ ነበር። ይህ ፊልም አሁንም ድረስ የተሰራበት ዘመን ይዞት ከተነሳው ሀሳብ አንፃር ጉሩም የሚያስብል ነው። ፊልሙ ጊዜውን ጠብቆና የአሜሪካን ነባራዊ ሁኔታ አንስቶ የሚተች ነው። በጊዜው በሀገረ አሜሪካ ጥቁሮች ላይ ከፍተኛ የሆነ የዘር ጥላቻና መገለል የነበረበት ነው። ሬግናልድ ሮስ በወቅቱ የነበረውን ዘረኝነት ከሰው ልጅ ሞራል አንፃር አዋህዶ በመፃፍ ለፊልም አብቅቶታል።

የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ በዛው ወቅት በአሜሪካ ምሁራን ዘንድ የተለያዩ የጥበብ ስራዎችን ከዘረኝነት የነፃ ለማድረግ ያመጡት የሂስ ፅንሰ ሀሳብ ነው። 12 አንግሪ ማን በትርጉም ስሙ 12ቱ እንግዶች በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ የዚህን ትርጉም ቴአትር ከሞራላዊና ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር በአመክንዮ ለመተንተን ተሞክሯል።

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ሞራላዊ የሆነ እና ከዘረኝነት የነፃ ማህበረሰብ ይፈጠር ዘንድ ኪነጥበብ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው እርግጥ ነው። ሞራላዊ ሂስ ፅንሰ ሀሳብ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ360 ዓ.ዓ ጀምሮ በኪነጥበብ ተድላዎች ይበልጥ ደግሞ በስነ-ፅሁፍ ውስጥ በአርስቶትልና ፕሌቶ መሀል በነበረው ክርክር ኪነጥባዊ ፋይዳው በብዙ አመክንዬች ሲታሰብ ኖራል። ነገር ግን በዘመን ሂደት ውስጥ ሞራላዊነት በኪነጥበብ ስራዎች ውስት እየተንፀባረቀ የግለሰቦችን፤ የማህበረሰብን፤ የፖለቲካ፤ የባህልን ሞራላዊ እሳቤ እየተካተተ ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብነቱ ተቀባይነት አግኝቷል።

የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ ( critical race theory ) በኪነጥበብ ስራዎች ላይ በተለያዬ መልኩ ( በኑሮ ደረጃ፤ በባህል፤በብሄር፤ በፆታ ) የሚንፀባረቁ የዘረኝነት ገፅታዎችን የሚመረምር ንድፈ ሀሳብ ነው። የአሜሪካ ምሁራኖች በሀገሪቱ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደረሶ የነበረውን ዘረኝነት በተለያዩ ተቋማትና የኪነጥበብ ዘርፍ ይተቹት ዘንድ ይህን ፅንሰ ሀሳብ በ1960ዎቹ ተግባር ላይ አዋሉት። ይህ ንድፈ ሀሳብ አለም አቀፍ በመሆን የተለያዩ ሀገራት እየተጠቀሙበት ይገኛል።

12ቱ እንግዶች ተውኔትም በእነዚህ ፅንሰ ሀሳቦች ላይ መሰረት ያደረገ ተውኔት ነው። በእርግጥም ዋናው ደራሲ በነበረት ዘመንና ማህበራዊ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ ቢፅፈውም ሀሳቡ ግን አለም አቀፍ ( universal ) የሆነ ወይም የትኛውንም ማህበረሰብ የሚወክል ፅንሰ ሀሳብን የያዘ ነው። ደራሲው በሀገረ አሜሪካ በሚያነሳው አከራካሪ የሆኑ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዬች ይታወቃል። በ ስራዎቹ ገፀ ባህሪያትን አላብሶ በሚያነሳቸው ሀሳቦች ተመልካቹን በእያንዳንዱ ገፀባህርይ ሞራላዊ ፍርድ ውስጥ አስምጦ የማብሰልሰል ሀይል እንዲኖረው አድርጓል። አስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት አጥኚው ከሁለቱ የሂስ ፅንሰ ሀሳቦች አንፃር ለማጥናት ሲነሳ የተውኔቱን ይዘት፤ ዘውግ፤ እና የሚያነሳቸው ማህበራዊ፤ ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ከግምት በማስገባት ለጥናቱ እንዲመቸው በማድረግ ይህን ቴአትር በተነሳውን ፅንሰ ሀሳብ ላይ ለመተንተን አነሳስቶታል።

## 1.2 የጥናቱ አላማ

### 1.2.1 የጥናቱ አብይ አላማ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አብይ አላማ 12ቱ እንግዶች ትርጉም ቴአትርን ከሞራላዊ ( morality ) እና ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ ( critical race theory ) አንፃር መተንተን ነው።

### 1.2.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ

- ✓ የተውኔትን ምንነት መግለፅ
- ✓ ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳቦችን ማሳወቅ
- ✓ ሞራላዊና የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብን መተንተን

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

- ✓ በተውኔቶቻቸው ውስጥ በተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች ላይ ተመርኩዘው የሚፅፉ ፅሀፈ ተውኔቶች ለመፍጠር ያግዛ
- ✓ ለሌሎች ጥናታዊ ፅሁፎች እንደመነሻ እና እንደ ተዛማጅ ፅሁፍነት ያገለግላል።

## 1.4 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች፦

- ❖ ሞራልና የዘር ሂሳዊ ንድፈ ሀሳቦች ለምንና እንዴት ተፈጠሩ? ምንድን ናቸው?
- ❖ አስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር እንዴት ተፅፏል?
- ❖ አስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት ከሞራል ሂሳዊ ጽንሰ ሀሳብ አንፃር እንዴት ተፅፏል?
- ❖ ተውኔቱ ከሁለቱ ፅንሰ ሀሳቦች አንፃር ለማህበረሰቡ ያለው ጠቀሜታ ምን ይመስላል?

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ትኩረቱን ያደረገው በአሜሪካዊው ደራሲ ሬግናልድ ሮስ የተፃፈውን የፊልም ፅሁፍ በሸርማን ኤልሰርግይ ወደ መድረክ ቴአትር ተለውጦ በአዲስ ተስፋ ወደ ሀገራች የተተረጎመውን 12ቱ እንግዶች ተውኔት ከሞራልና ከዘር ሂሳዊ ፅኝሰ ሀሳብ አንፃር መተንተን ነው።

## 1.6 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ገላጭ ከሚባለው የጥናታዊ ፅሁፍ አይነት በመጠቀም የቀረበ ሲሆን። አጥኝው ይሄንን የምርምር ዘዴ የመረጠበት ምክንያት ለጥናታዊ ፅሁፍ ለተመረው ርዕስ አመቺ ሆኖ ስላገኘው ነው። “መሰረታዊ የምርምር ዘዴዎች" በተሰኘው የአለም እሸቱ በተሰኘው መጽሃፍ ላይ ተገልጿል። “ገላጭ ጥንታዊ ፅሁፍ በሁለት ተለዋዋጮች መካከል የሚኖረውን? ተዛምዶ እያነፃፀረ የሚተነትን የጥናታዊ ፅሁፍ አይነት ነው" (አለም እሸቱ፤2001፤148) አጥኚውም በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ "12ቱ እንግዶች" ተውኔትን ከሁለቱ የሂሳዊ ንድፈ ሀሳቦች ዙሪያ እያነጻጸረ ለመተንተንና ለሁለቱም ጽንሰ ሃሳቦች አመች ሁኖ ስላገኘው ይህንን የአጠናን ዘዴ ተጠቅሞበታል።

### 1.6.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

አጥኚው ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ ለመስራት ከተለያዩ ምንጮች ያገኛቸውን የተለያዩ መረጃዎችን ተጠቅሟል። በዚህም መሠረት ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭ ከምንላቸው ውስጥ በዋናነት የአስራ ሁለቱ እንግዶችን ፅሁፈ ተውኔት የተጠቀመ ሲሆን እንዲሁም በተለያዩ ሰዎች የተፃፉ የተለያዩ መፅሐፍትን፣ ጋዜጦችን፣ መፅሔቶችን፣ ጥናታዊ ፅሁፎችን፣ ድህረ ገፆችን… ወዘተ የተጠቀመ ሲሆን፤ ሦስተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭ ከምንላቸው ደግሞ ሌሎች ሰዎች የተጠቀሟቸውን ዋቢ መፅሐፍት በመጠቀም ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ አቅርቧል።

## 1.7 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናታዉ ፅሁፍ በአራት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን፦

በምዕራፍ አንድ መግቢያ፤ የጥናቱ ዳራ፤ የጥናቱ አላማ፤ አብይ እና ንዑስ አላማ፤ የጥናቱ ጠቀሜታ፤ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች፤ የጥናቱ ወሰን፤ የጥናቱ ዘዴ፤ የጥናቱ አደረጃጀት፤ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች፤ እና በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ይገኛሉ። በምዕራፍ ሁለት ደግሞ የንደፈ ሀሳብ ቅኝት የሚገኝ ሲሆን በምዕራፉም ስለ ተውኔት፤ ሂስ፤ የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ፤ የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ መርሆች፤ የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ በኪነጥበብ ስራዎች እና በአጠቃላይ ስርዓቶች ላይ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች፤ የሞራል ፍልስፍና፤ ሞራላዊ ሂስ፤ ሞራላዊ ሂስ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች እና የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት ናቸው።

በምዕራፍ ሶስት ደግሞ የመረጃ ትንተና የሚገኝ ሲሆን በምዕራፉም የአስራ ሁለቱ እንዶች ተውኔት ታሪክ፤ ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ትንተና፤ ከዘረኝነት አንፃር የገፀባህሪያት አሳሳል፤ ተውኔቱ ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ለማህበረሰቡ ያለው ጠቀሜታ እንዲሁም ከፅንሰ ሀሳቡ አንፃር የተለያዩ ጥንካሬዎችና ድክመቶች ተገልፀዋል። በሌላኛው ርዕስ ደግሞ አስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት ከሞራላዊ ሂስ አንፃር፤ ገፀባሕርያቱ ከሞራላዊነት አንፃር እንዴት እንደተሳሉ፤ ተውኔቱ የሚያነሳቸው ሞራላዊ እሳቤዎች፤ ተውኔቱ ከሞራላዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ለማህበረሰቡ ያለው ጠቀሜታ እንዲሁም ከሞራላዊ

ሂስ አንፃር ጠንካራና ደካማ ጎኖች ተገልፀዋል። ምዕራፍ አራት ደግሞ ማጠቃለያ፤ የመፍትሄ ሀሳቦች፤ ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው እና ዋቢ መፅሀፍትን አካቶ ይገኛል።

## 1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ወቅት ካጋጠሙ ችግሮች መካከል የመጀመሪያው ጥናቱ የተሰራበት ተውኔት አዲስ መሆን ነው። አጥኝው በዚህ ተውኔት ላይ ጥናታዊ ፅሁፍ ለማዘጋጀት ተውኔቱ ለዕይታ የሚቀርብበትንና የዩኒቨርስቲውን አመታዊ የት/ት እቅድ በማገናዘብ ነበር። ነገር ግን የተውኔቱ ምርቃት መራዘም ጥናታዊ ፅሁፉ እንዳይጓተት አጥኝውን ስጋት ላይ ሊጥለው ችሏል። ቢሆንም ተውኔቱ ትርጉም እንደመሆኑ አጥኝው በዋናው ተውኔት ላይ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ እንደ መፍትሄ ተጠቅሟል።

ሌላኛው በጥናቱ ወቅት ያጋጠመው ችግር ደግሞ በቂ የሆኑ ዋቢ መፅሀፍቶችን አለማግኘት እና ጥናቱ ስለተነሳበት ፅንሰ ሀሳብ በኢትዮጵያውያን ፀሀፊዎች የተዘጋጀ ዋቢ መፅሀፍ አለማግኘቱ እንዲሁም ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሌሎች ጥናታዊ ፅሁፎችን አለማገኘታቸው ነው። ለዚህም እንደ መፍትሄ ሀሳብ ከተለያዩ የኢንተርኔት ድረገፆች ላይ ከጥናቱ ጋር ተያያዝ የሆኑ መፅሀፍትን እና ጥናታዊ ፅሁፎችን አጥኝው ተጠቅሟል።

## ምዕራፍ ሁለት

## 2. የንድፈ ሀሳብ ቅኝት

### 2.1 ተውኔት

ስነፅሁፍ በውስጡ የተለያዩ ዘውጎችን የያዘ የኪነ ጥበብ አይነት ነው። ከእነሱም መሀል ተውኔት አንዱ ሲሆን እንደሌሎች የስነፅሁፍ አይነቶች በውስጡ በርካታ ቅርፆችን እና ባህርያትን አካቶ ይይዛል። ከጥንትም ጀምሮ የራሱን ቅርፅና ጥበባዊ ውበት እየያዘ የመጣ የኪነጥበብ ዓይነት ነው።በመጀመሪያ ተውኔት የሚለው ቃል ፍች(ትርጉም) የሻው ተሰማ "የተውኔት አፅናፍ መነፅር" በሚለው መፅሀፉ ሲገልፀው፦

> "ተውኔት የሚለውን ቃል «drama» የምንለውን እሳቤ እንዲወክል ያደረግነው ከግእዙ ተውስን ነው፡፡ ኪዳን ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ስዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት አዲስ በተባለው ሥራቸው በገጽ 894 ላይየተውኔትን ግስ ፍች ሲገልጹት፣ «ተዋነየ፤ተጫወተ» በማለት አስቀምጠውታል፡፡ እንደገናም «ተዋነየ»ን በሌላ ገጽ ሲፈቱት፣ «ተጫወተ፣ ተጨዋወተ፣ ተነጋገረ፡፡» እያሉ በመሆኑ፣ ጭውውቱ የቋንቋንም አስፈላነጊነት የሚጠቁም ይመስላል። ከዚህ ጋር በማያያዝ ነው እኝሁ ሊቅ፣ «ተውኔት» የሚለውን ቃል በርባታ የሚያመለክቱን፤ «ጨዋታ፣ ዘፈን፣ በዙ ስምና ስልት መሳሪያ ያለው» (ገጽ 394) በማለት። ከዚህም በተጨማሪ፣ ዛሬ በተውኔት ትምህርታችን ውስጥ የምንጠቀም ባቸውን እንደ «ቃለ ተውኔት»፣ «ቤተ ተውኔት»፣ እና «ተዋናዪ»፣ የመሳሰሉትን የዛሬ ጽንሰሐሳብ መሥራች ቃላት፣ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ከዘመናት በፊት ባዘጋጁት መዝገበ ቃላት ውስጥ አስገብተዋቸው ይገኛሉ"(የሻው ተሰማ፤ 1998፤12)

የተውኔት አጀማመር ለማወቅ ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ ኋላ መመለስ እና ታሪክን መቃኘት ያስፈልጋል።በአለማችን ላይ ይከወኑ የነበሩ የአምልኮ ስርዓቶች እና በአላት የድራማ ባህሪ ነበራቸው ይህ በሂደቶች ብዛት ዛሬ ላይ እደደረሰ ይነገርለታል ።በአለማችህን የትያትር ተዉነት አጀማመር የየራሱ የእድገት ደረጃ አለዉ፡፡የመጀመሪያዉ በአመልኮ የተጀመረዉ በግሪክ ሲሆን አድጎ ወደ ሮም እደሄደና የራሳቸዉን ይዘቶች በመጨመር በማስፋፋት ወደ ለሎች ሀገራት ተስፋፍቷል። ደበበ ሰይፉ "የቴአትር ጥበብ ከፅሀፈ ተውኔቱ አንፃር" በሚ"ለው መፅሀፉ ስለ ቴአትር ሲገልፅ፦

> የቲያትር ጥበብ የሰው ልጆች ሕይወት በመድረክ ላይ የሚገለጽበትና ሚተረጎምበት አንድ ዐቢይ የኪነጥበብ ዘርፍ ነው። ይህ ጥበብ መደቀኛ መልኩን አገኘ እሚባለው በግሪክ ሀገር ኣስኪሊስ "አቤት ባዮቹ" የተሰኘውን ተውኔቱን ባቀረበበት በ46 ዓ.ዓ. (እ. ኤ አ) ላይ ነው ቢባልም ፍንጩ ግን ከዚያ በፊት በነበረ ቀደምት ዘመን በጥንታውያን ግብፆች የመቃብር ሥርዓት ወግና በቅድመ ታሪክ ጥንታውያን ሕዝቦች የዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ይገኝ እንደ ነበር ይታወቃል(ደበበ ሰይፉ፤ 1973፤7)

**ተውኔት** ወይም ቴአትር በገቢሮችና በትዕይንቶች የተከፋፈለ እና የተለያዩ ዘውጎች፤ ቅርፆችና ባህርያትን የያዘ ሲሆን ፀሀፈ ተውኔቶች ለመፃፍ በፈለጉት ዘውግና ቅርፅ ተውኔቶችን ይፅፋሉ። አዘጋጆቹም የተለያዩ የዝግጅት ቴክኒኮችን በመጠቀም ለመድረክ ያቀርባሉ።

### 2.2 ሂስ

ኪነ ጥበብ ለጥበበኛው ብዙ አይነት ነፃነትን ያላብሳል። የተለያየ ማህበረሰባዊ ስርዓቶች እና የኪነጥበብ ስራዎች በምታስተናግደው አለም የጥበብ ሰዎች ባላቸው ጥበባዊ ነፃነት አስተሳሰቦቻቸውን፤ እምነታቸውን፤ በአጠቃላይ የውስጣቸውን መሻት ያንፀባርቃሉ። ሀያሲዎች ይህን ስራቸው ለማህበረሰብ ከሚያመጣው ጠቀሜታ አንፃር እና በራሱ በስራው ቅርፅ በተለየዩ ፅንሰ ሀሳቦች ሂስ በመስጠት ለኪነጥበብ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። ሂስ የጀመረው በጥንታዊያን ግሪኮች ሲሆን በጊዜው የነበሩት የፅንስ ሀሳብ ሰዎችና ፈላስፋዎች በሂስ አሰጣጥ ስርዓት ላይ በራሳቸው አመለካከት ሲከራከሩበትና የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦችን እየፈጠሩ ሂስን እስከ እዚህ ዘመን ድረስ አሸጋግረውታል። ሂስ ማለት አንድን ነገር በጥንቃቄ መገምገም፣ መተንተን ማለት ነው። ሂስ በሥነ ጽሑፍ፣ በኪነ ጥበብ፣ በፊልም፣ በሙዚቃ፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ ጉዳዮች እና በሌሎችም መስኮች ላይ ሊተገበር ይችላል። ሂስ ሁል ጊዜ ስህተቶችን ብቻ እያወጣ እና እየወቀሰ ሳይሆን ጥሩ ጎነችን

እያበረታታና ስህተቶቹን ትህትና በተላበሰ መልኩ ማሻሻያ እንዲደረግባቸው ከፅንሰ ሀሳቦች አንፃር የሚተነትን ነው። ፈንታሁን እንግዳ " ስብስብ" በሚል ርዕስ በፃፈው መፅሀፉ ላይ ስለ ሂስ ሲገልፅ:-

> ሆልማን እንደሚያብራራው ሂስ የሚተነትን የሚያነፃፅር የሚተረጉም እና እንዲሁም የየግለሰቦችን ፈጠራ ከአጠቃላይ የኪነ ጥበባዊ መለኪያዎችና ሥነ-ውበት አንፃር የሚመዝን ጥበብ ነው። ይህ የኪነ ጥበብ ሣይንስ የተጀመረው በጥንታዊው የግሪክ ዘመን ሲሆን ለእኛ ዘመነኞች ተላልፈዋል ተብሎ ከሚታመንባቸው መካከል የአሪስጣጣሊስ እና የአፍላጦን ተውኔታዊ እና ሥ-ጽሑፋዊ ሂሶች ይገኙበታል(ፈንታሁን እንግዳ፤ 2007፤ 27)

የሂስ ዋና ዓላማ አንድን ነገር በጥልቀት በመረዳት፣ ጥንካሬውን እና ድክመቱን በመለየት እና ስለ ጉዳዩ የተሻለ ግንዛቤ ማግኘት ነው። ሂስ ገንቢ ሊሆን ይችላል፣ ይህም የአንድን ነገር ጉድለቶች በመጠቀም እና እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል ሃሳቦችን በማቅረብ ላይ ያተኩራል። እንዲሁም፣ ሂስ አጥፊ ሊሆን ይችላል፣ ይህም በአንድ ነገር ላይ አሉታዊ ጎኖቹን ብቻ በማጉላት እና ምንም ጠቃሚ አስተዋጽኦ ሳያደርግ ሲቀር ማለት ነው።

ጥሩ ሂስ የሚከተሉትን ባህሪዎች ሊኖረው ይገባል:-

- ❖ ተጨባጭነትን: በግል አስተያየቶች ወይም ስሜቶች ላይ ሳይሆንበተጨባጭ ማስረጃዎች እና እውነታዎችላይ የተመሰረተ አለበት።
- ❖ ምክንያታዊነትን: ምክንያታዊ በሆነ መንገድ መቅረብ አለበት።
- ❖ አሳማኝነትን: አሳማኝ በሆኑ ክርክሮች እና ማስረጃዎች መደገፍ አለበት።
- ❖ ግልጽነትን: በቀላሉ ሊረዳ በሚችል ቋንቋ መቅረብ አለበት።
- ❖ አክብሮትን: ትችቱ ገንቢ እና አክብሮት በተሞላበት መንገድ መቅረብ አለበት።

ሂስ ለግለሰቦች እና ለህብረተሰቡ ብዙ ጥቅሞችን ሊያመጣ ይችላል። ለምሳሌ፣ ሂስ አንድን ነገር በማሻሻል፣ አዲስ እውቀት በመፍጠር፣ የፈጠራ ችሎታን በማነቃቃት እና የውይይት እና የክርክር ባህልን በማዳበር ላይ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል። የተለያዩ የሂስ ፅንሰ ሀሳብ ሰዎችና ትምህርቶች ብዛት ያለው የሂስ አይነቶችን የተለያዩ ገለፃዎች ቢኖሯቸውም ፈንታሁን እንግዳ የገለፃቸውን ስንመለከት "ስሜተ- ግቡዕ ሂስ (ኢምፕሬሽኒስት)፤ ታሪካዊ ሂስ፤ ፅሁፋዊ ሂስ፤ ቅርፃዊ ሂስ፤ ዜና መዕዋላዊ ሂስ (ህይወት ታሪክ)፤ ንፅፅራዊ ሂስ፤ ግብረ-ገባዊ ሂስ፤መዋቅራዊ ሂስ፤ ንድፈ-ሀሳባዊ ሂስ"(ፈንታሁን እንግዳ፤2001፤30-32) በማለት ይገልፃቸዋል።

እነዚህ ንድፈ ሀሳቦች እንዲሁም ከጊዜያት በኋላ የተመሰረቱ ጽንሰ ሃሳቦች ከተጠነሰሱበት ዘመን ጀምሮ እስካሁን ድረስ በሀያሲዎች የሚተገበሩ ሲሆኑ ምሁራኖቹም በዘመን ሂደት በእነዚህ ፅንሰ ሀሳቦች ዙሪ ሲከራከሩባቸውና በመዋቅሮቻቸው፤ በቅርፃቸው እሳቤያቸውን ሲጨምሩና ሲቀንሱ እዚህ ደርሰዋል።

## 2.3 የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ

ዘረኝነት በሰው ልጅ ጓዳ ውስጥ ስሩን የሰደደ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ዘረኝነት በሰው ልጆች ላይ በተፈጥሮ እና በማህበራዊ እሳቤዎች ላይ በመመርኮዝ ሊፈጠር ይችላል። በግለሰብና በቡድን ደረጃ የዘረኝነት ሰለባ የሚሆኑት በብሄሮቻቸው፤ በፆታዎቻቸው፤ በቆዳ ቀለማቸው፤ በዘሮቻቸው ሲሆን በተፈጥሮ ደረጃ የዘረኝነት ሰለባ ተጠቂዎች ይሆናሉ። በማህበራዊ ኑሯቸው፤ በኑሮ ደረጃቸው፤ በሚከተሉት የፖለቲካ አቋም፤ ወ.ዘ.ተ በአኗኗር ውስጥ በሚገነቡ ማንነቶች ላይ የዘረኝነት ተፅእኖ ውስጥ ይወድቃሉ።

በኒዎርክ ዩኒቨርሲቲ የህግ ፕሮፌሰር የነበሩት ዴሪክ ቤል የንቅናቄው አባት በመባል ይታወቃሉ። ፕሮፌሰሩ አሜሪካ ውስጥ የሚመለከቱት ዘረኝነት ይበልጥ ደሞ በህጉ ዙሪያ ለሚደርሱ ኢ-ፍትሀዊ አሰራሮች ቅርብ ከመሆናቸው የተነሳ በዚህ

ዙሪያ የተለያዩ ወሳኝ ጥናታዊ ፅሁፎችን በማዘጋጀት ይታወቁ ነበር። ይህን ፅንሰ ሀሳብ ከመሰረቱት ምሁራኖች መካከል ሪቻረድ ዴልጋይ እና ጄን ስቴፈንሲስ ይገኙበታል።ሁለቱም በጋራ በፃፉት "ክሬቲካል ሬስ ቲዎሪ" በተሰኘው መፅሀፋቸው ላይ ስለ ዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ እንዲህ ሲሉ አስፍረዋል።

> የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ እንቅስቃሴ የተለያዩ ምሁራን በዘር ስርጭት፣ እና በሥልጣን መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጥናትና ለመቀየር የሚፈልጉ ስብስብን የያዘ ነው። ይህ እንቅስቃሴ በተለምዶ የሥርዓተ-ዜጋ መብትና የዘር ጥናት ውድድሮች የሚነካቸውን ብዙ ጉዳዮች ይመለከታል፤ ነገር ግን እነዚህን ጉዳዮች በኢኮኖሚ፣ ታሪክ፣ የማዕቀፍ ሁኔታ፣ የቡድንና የግል ፍላጎት ጫና ውስጥ በመርመር ይመለከታል። 1[nd] (ሪቻርድ ዴልጋዶ እና ጄን ስቴፈንሲስ፤ 1992.1)

ይህ ማለት የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ በሰው ልጆች ዘር እና ስልጣን መካከል ያለውን ግኑኝነት ለማጥናትና ፍትሀዊ ለማድረግ ፍላጎት ያላቸው የተሟጋቾችና የምሁራን ስብስብ መሆኑን ይገልፃል። ንቅናቄውም የተለያዩ የመብትና የጎሳ ጥያቄዎችን እያነሳ የተለያዩ ጉዳዮችን የኢኮኖሚ፤ የታሪክ፤ የቡድን ሆነ የግል ጥቅሞችን፤ ፖለቲካዊ አውዶችን እያነሳ እንደሚመረመር ይገልፃል። በጊዜው በአሜሪካ በዋነኝነት ስልጣን በነጮች የበላይነት ነበር። ጥቁሮች ወይም በጊዜው ከተለያዩ ሀገራት የመጡ ኗሪዎች እንዲሁም አሜሪካዊ ሆነው የኑሮ ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆኑ ሰዎች በሚደርስባቸው ጫና የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ በትኩረት ይሰራል።

> የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አላማው መጀመሪያ የነጮችን የበላይነት አገዛዝና የበታች ቀለም ያላቸው ሰዎች በአሜሪካ ውስጥ እንዴት እንደተፈጠሩና እንዴት እየተጠበቁ እንደሆነ መረዳትና በዚያ ማህበራዊ መዋቅርና የአገዛዝ ስርዓት እሳቤዎች መካከል ያለውን ግኑኝነት መመርመር ነው። 2[rd] (ቶማስ.ፔለር. ጎታንዳ፤ 1983. 2 )

## 2.3.1 የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አምስቱ መርሆች

የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ ላይ ምሁራኖቹ የሚስማሙበት አምስት መርሆች ሲኖሩ እነሱም፡-

- ዘረኝነት በቀለም ዘር ሰዎች የለመደ ልምድ ነው።
- በአሜሪካ ያሉ የዳኝነት እና የፖለቲካ ስርዓቶች በተፈጥሯቸው ዘረኝነት አለባቸው።
- ህጎች ገለልተኛ ናቸው ብሎ ማሰብ ወደ መድልዎ ያመራል።
- ዘር ማህበራዊ ግንባታ ነው።
- የነጭ ምሁራን አንድ ነገር የሚያደርጉት ለእነሱ ጥቅም ካገለከለ ብቻ ነው። 3[th] (www.studysmarter.co.uk )

የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ መነሻው አሜሪካ ውስጥ በጥቁሮች የሚደርሰው ዘረኝነት ጥቃቶች ቢሆንም ይህ እንቅስቃሴ እየሰፋ ሂዶ በአጠቃላይ የቀለም ልዩነት መሰረት ያደረጉ፤ የኑሮ መደብን፤ ብሄርን፤ ወ.ዘ.ተ ማንኛውም ዘረኝነትን ከተቋማት፤ ከኪነ ጥበብ ስራዎችና ከተለያዩ እሳቤዎች አንፃር ሂስ ይሰጣል። ITAC "የፀረ ዘረኝነት ልምምድና የአርቲስቶች ተጠቃሚ መመሪያ" በሚል ርዕስ ከዘረኝነት የነፃ የኪነ ጥበብ ስራዎች እንዲፈጠሩ እንዲያግዝ በድህረ ገፃቸው በለቀቁት ጥናታዊ ፅሁፋቸው ስለ ዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ ሲገልፁ " የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ ዘረኝነት በማህበራዊ ግንባታ እንደታነፀ የሚመለከት ፅንሰ ሀሳብ ነው። እንዲሁም ዘረኝነት ለግለሰቦች፤ በተቋሞች እና በመዋቅሮች የሚቀጥል ነው"(https://manuals.plus)

## 2.3.2 የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ በኪነጥበብ ስራዎች እና በአጠቃላይ ስርዓቶች ላይ ሚያነሳው ጥያቄ

በተለያዩ የኪነጥበብ ስራዎች ላይ ማለትም በፊልም፤ በሙዚቃ፤ በድራማ፤ በቴአትር፤ በስነ ፅሁፍ ስራዎች፤ ስዕሎ ወ.ዘ.ተ የሰው ልጆች እንደየ አመለካከታቸው ዘረኝነትን ነቅፈው ወይም ደሞ የራሳቸውን የዘረኝነት ስሜቶች ለማስተላለፍ ኪነጥበብን ይጠቀሙበታል። ኪነ ጥበብ ተደራሽነቱ ሰፊ ስለሆነ የተለያዩ ማህበረሰቦችን ስሜት ገዝቶ በስራዎቹ የማነሳሳትና የመጣል አቅም አለው። ሰለ ዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ በተፃፉ መፅሀፍቶች፤ የመማሪያ መፅሀፍቶች፤ ወይም ጥናታዊ ፅሁፎች ላይ እንደ ርዕስ እራሱን ችሎ በኪነ ጥበብ ስራዎችና ማህበረሰባዊ ስርአቶች የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ባይሰፍሩም ሁሉም መዛግብትና የፅንሰ ሀሳቡ ምሁራኖች የሚስማሙባቸው ጥያቄዎች አሉ። እነሱም፡-

- ዘረኝነት በበላይነት በሆነው አካል ውስጥ የሚታየው፤ የሚቀረፀው፤ የሚንፀባረቀው በየት፤ በምን መንገድ እና በምን አላማዎች ነው?
- የበላይ የሆነው አካል ስለ ዘር ያለውን አመለካከት የሚያንፀባርቀው በምን አይነት መንገድ ነው ?
- ዘረኝነት ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች የሚመለከት ስጋት መሆኑን ምሁራኖች ወይም የኪነ ጥበብ ሰዎች እንዴት ያስተላልፋሉ?
- የዘረኝነት ሰለባ የሆኑ ተሞክሮዎች በትክክል ተንፀባርቀዋል ወይ?
- በኪነ ጥበብ ስራዎች ላይ በዘረኝነት የጨቆነው ወይም የተጨቆነው አካል ማን ነው?
- በኪነ ጥበብ ስራው ላይ የገሀዱን አለም የወከሉ ገፀ ባህሪያት በዘረኝነት ዙሪያ እንዴት ተስለዋል?
- የኪነጥበብ ስራው በትክክል ተቋሞች ወይም ስርዓቶች ላይ የሚንፀባረቀውን ዘረኝነት ይተቻል?

5th (www. Scholarship.law.nd.edu.com)

## 2.4. ሞራላዊ ሂስ

ከሂስ አይነቶች መካከል አንዱ የሆነው ሞራላዊ  ሂስ ከነፕሌቶ ጀምሮ በብዙ ሃያሲን ዘንድ በተግባር ላይ ይውል የነበረና የረጂም ዘመን ዕድሜ ያለው የሂስ አይነት ነው፡፡ ዋነኛ ትኩረቱም አንድ ሥነ-ጽሁፋዊ ስራ ይዞት በተነሳው ወይም ሊያስተላልፈው በፈለገው ቁም ነገር ላይ ነው። በዚህም ሂስ በብዛት ወይም በሰፊው የስነ ፅሁፍ ስራዎች ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሰራበታል።ረጅም እና አጭር ልብ ወለዶች፤ ወጎች፤ ግጥሞች የህይወት ታሪኮች ላይ ሀያሲዎች በሰፊው ከሞራል አንፃር ሂስ ይሰጡበታል። "ግብረገባዊ ሂስ - አንድ ሃያሲ ማንኛውንም የፈጠራ ውጤት ከሰው ልጅ ሕይወት የአኗኗር ባህል፣ እምነት፣ አስተሳሰብ፣ ወዘተ እሴት አንጻር ሰብአዊ እና ምናባዊ የሆነ አላባውያን ተጥሰው ወይም ገዝፈው መቅረባቸውን የሚመዝን ሂስ ሲሆን እንደሌሎቹ ሁሉ ራሱ መለያ ባህሪ አለው፡፡ ከሌሎቹ የሂስ ዓይነቶች እንዲለይ የሚያደርገው አጥብቆ ህሊናዊነት የሚያጠቃው መሆኑ ነው" (ፈንታሁን እንግዳ፤ 2007፤ 31)

ሞራላዊ ሂስ በኪነ ጥበብ ስራዎች ላይ አስፈላጊ ሚና ይጫወታል። የኪነ ጥበብ ሰዎች በተለያዩ የኪነጥበብ መስኮች( ሥነ ፅሑፍ፣ ሥነ ሥዕል፣ ቲያትር፣ ፊልም፣ ሙዚቃ ወይም ሌሎች የሥነ ጥበብ መልስዎች) የህብረተሰቡን ሞራል፣ ሃሳብ፣ እና ስሜት ለመግለጽና እዲሁም የራሳቸውን እሳቤዎች ለማስተላለፍ ይጠቀማሉ። በሞራላዊ ሂስ የሚሰጡ ሀያሲያን ሞራላዊ ሂስ ከሚያነሳቸው ጥያቄዎች አንፃር የኪነ ጥበብ ስራው ላይ ሂስ በመስጠት አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።

> ስነ-ምግባራዊ ሂስ የሚያደርግ ሃያሲን የሚያስጨንቀው በስራው ምን ተባለ፣ ምን ቀረበ የሚለው ነው፡፡ እንዴት ቀርበ የሚለው ግን አያስጨንቀውም፡፡ በዚህ አይነቱ ሂስ የስነ-ጽሑፋዊ ስራዎች ድክመት ጥንካሬ የሚዳኘው ስራው ከሚያንፀባርቀው የዘመኑ ስነ-ምግባር አንፃር ነው፡፡ በዘመኑ በታወቁ ስነ-ምግባራዊ መርሆዎችጰበመሳሰሉት ስራው ምን ያህል ሰዋዊነት እንደሚንፀባረቅበት ይመዘናል፡፡ ስራው የዚያን ዘመን የስነ-ምግባር መርሆዎች ምን ያህል እንዳንፀባረቀ ስነ-ምግባራዊ መርሆዎች መሰረት አድረጎተ ለማህበረሰቡ የሚጠቅም ጉዳይ ማበርከቱና አለማበርከቱ ይመረምራል፡፡ ሂሱም በዚህ ዙሪያ

የሚያጠነጥን ይሆናል፡፡ አንድ አንባቢ ከፈጠራ ስራዎች ስለህይወት ምን ሊማር ይችላል? ከታሪኩ አንባቢው ምን ያክል መልካም ምግባራትን ያወርሳል? የሚሉትን ያጠናል፡፡ ባጠቃላይ የዚህ ሂስ ዋና አላማ የስነ ጽሑፍ ስራው ምን ያክል ስነምግባራዊ እሴቶችን እንደሚያንጸባርቅ መመርመር ነው፡፡ ሂሱ ቀዳሚ የሂስ አይነት ቢሆንም ብዙ ነቀፍታዎች ገጥመውታል፡፡ ከነዚህ መካከል ከውበታዊነት ወይም ኪናዊነት ይልቅ ይዘት ላይ ብቻ ማተኮሩ የስነ ጽሑፍ ውበታዊ ፋይዳ እንዳይታ አድርጓል የሚለው አንዱ ነው፡ 5th (http//: eopcw.com )

## 2.4.1. ሞራላዊ ሂስ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

እንደ ሌሎች የሂስ ፅንሰ ሀሳቦች ሞራላዊ ሂስም በተለያዩ ማህበራዊ ስርዓቶችና የኪነጥበብ ስራዎች ላይ ወሳኝ ጥያቄዎችን በማንሳት ሂስ ይሰጣል።

- የሥነ ምግባር ይዘት እና መልእክት- የኪነ ጥበብ ሥራው ምን ዓይነት የሥነ ምግባርእሴቶችን እና መልእክቶችን ያስተላልፋል? በውስጡ የተካተቱት ሐሳቦች እና ድርጊቶች በሥነ ምግባር ትክክል ናቸው ወይስ አይደሉም?
- የገጸ-ባህሪያት ሥነ ምግባር- በኪነ ጥበብ ሥራው ውስጥ ያሉ ገጸ-ባህሪያት በሥነ ምግባር እንዴት ይገለፃሉ? የነሱ ባህሪያት እና ድርጊቶች ተመልካቾች ወይም አንባቢዎች ላይ ምን ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ?
- የኪነ ጥበብ ሥራው ተጽዕኖ- የኪነ ጥበብ ሥራው በህብረተሰብ ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል? ለሥነ ምግባር ብልሹነት ወይም የተሳሳቱ አመለካከቶችን ሊያበረታታ ይችላል?
- የአርቲስቱ ኃላፊነት- አርቲስቱ በሥነ ምግባር ይዘት ያላቸውን ሥራዎች የመፍጠር ኃላፊነት አለበት? የኪነ ጥበብ ነፃነት እና የሞራል እሴቶች መካከል ያለው ሚዛን እንዴት መሆን አለበት?
- ደራሲው በስራው ውስጥ በገፀ-ባህሪያት በሴራ ወይም በጭብጥ የሚያቀርበው የትኛውን የሞራል ትምህርት ነው? የሞራል መርሆችንስ እንዴት ይወክላል?
- የኪነ ጥበብ ስራው ሞራላዊ ትምህርት ወይም ፍልስፍናዊ ሀሳብ ያቀርባል? 6th(http//:www.prezi.com)

ቅንነት፤ ታማኝነት፤ ሀቀኝነት፤ ሰው አክባሪነት፤ ወ.ዘ.ተ የሞራል እሴቶች ተብለው የሚጠቀሱት አንድን ስነ ፅሁፍ ወይም ደግሞ የኪነ ጥበብ ስራዎችን ለመስራት ከማስፈለጋቸውም በላይ የጥበባዊ ዋጋ ከፍ እንዲል ጉልህ ሚና ይጫወታሉ።

## 2.5 የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት

ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሁለት በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ለባችለር ድግሪ የቀረቡ ጥናታዊ ፅሁፎች ይገኛሉ። የመጀመሪያው በሸዋን ግዛው መንግስቴ የተዘጋጀው "ጁሊስ ቄሳር ተውኔት ከኒው ሂስቶሪሲዝም አንፃር" የተሰኘው ጥናታዊ ፅሁፍ ሲሆን ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በ 2011 ዓም የቀረበ ነው። በዚህም ጥናታዊ ፅሁፍ በምዕራፍ አንድ መግቢያ፤ የጥናቱ ዳራ፤ የጥናቱ አላማ፤ አብይ እና ንዑስ አላማ፤ የጥናቱ ጠቀሜታ፤ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች፤ የጥናቱ ወሰን፤ የጥናቱ ዘዴ፤ የጥናቱ አወቃቀር፤ የመረጃ ምንጮች፤ እና በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ይገኛሉ። በምዕራፍ ሁለት ደግሞ ክለሳ ድርሳናት፤ የተውኔት ምንነት፤ የታሪካዊ ተውኔት ምንነት እና ፋይዳዊ፤ መቼት፤ ገፀባሕርያት፤ የግጭት አወቃቀር በታሪካዊ ተውኔት፤ የሂስ ምንነት፤ የኒው ሂስቶሪሲዝም ምንነት፤ አጀማመር እና እደገት እንዲሁም የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ይገኙበታል። በምዕራፍ ሶስት የመረጃ ትንተና እና በምዕራፍ አራት ደግሞ ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳብ ይገኛል። የሁለቱም ጥናታዊ ፅሁፎች ተዛማጅነት ሁለቱም በተውኔቶች ላይ መስራታቸው፤ በሂሳዊ ትንተና ማቅረባቸውና በአራት ምዕራፎች መዋቀራቸው ነው። ልዩነታቸው ደግሞ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በ"12ቱ እንግዶች" ተውኔት ሲሰራ ሌላኛ ግን በጁሊስ ቄሳር

ተውኔት መሰራቱ ነው። እንዲሁም ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከሞራላዊ እና ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ሲሰራ ሌላኛው ደግሞ በኒው ሂስቶሪሲዝም ሂስ የተሰራ መሆኑ ነው።

ሁለተኛው ተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፍ ደግሞ በዮናስ እሸቱ የተዘጋጀው "የልምዣት ከማርክሲዝም ፅንሰ ሀሳብ አንፃር" የተሰኘው በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ በ2010 ዓም ለባችለር ድግሪ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ነው። በምዕራፍ አንድ መግቢያ፤ የጥናቱ ዳራ፤ የጥናቱ አላማ፤ አብይ እና ንዑስ አላማ፤ የጥናቱ ጠቀሜታ፤ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች፤ የጥናቱ ወሰን፤ የጥናቱ ዘዴ፤ የጥናቱ አደረጃጀት፤ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች፤ እና በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ይገኛሉ። በምዕራፍ ሁለት የንድፈ ሀሳብ ቅኝት፤ የማርክሲዝም ፅንሰ ሀሳብ ምንነት፤ ስነፅሁፋዊ የሂስ ንድፈ ሀሳብ፤ ስነፅሁፍ እና ርዮተ አለም(ማርክሲዝም)፤ ሶሻሊስት ሪያሊዝም፤ የስነፅሁፍ አበይት ክፍሎች፤ የልብወለድ ፅንሰ ሀሳብ ምንነት እና የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት ይገኛል። በምዕራፍ ሶስት የመረጃ ትንተና እና በምዕራፍ አራት ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች ይገኛሉ። ሁለቱም ጥናታዊ ፅሁፎች ያላቸው ተዛማጅነት ሁለቱም ከሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር መዘጋጀታቸውና በአራት ምዕራፎች መዋቀራቸው ነው። ልዩነታቸው ደግሞ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በተውኔት ስራ ላይ ሂሳዊ ትንተና ሲሰጥ ሌላኛው ደግም በረጅም ልብ ወለድ ስራ ላይ ሂሳዊ ትንተና መስጠቱ ነው። እንዲሁም ሌላ የሚለያቸው ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከሞራሊዝምና ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ሲዘጋጅ ሌላኛው ደግሞ ከማርክሲዝም ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ መዘጋጀቱ ነው።

## ምዕራፍ ሶስት

## 3. የመረጃ ትንተና

### 3.1 የአስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት ታሪክ

ፍርድ ቤት ውስጥ በመጀመሪያ ደረጃ የግድያ ወንጀል የተጠረጠረ የ19 አመት ወጣት የፍርድ ስርዓት ላይ ታሪኩ ይጀምራል። ወጣቱ ሽማግሌ አባቱን በጩቤ ወግተህ ገለህል ተብሎ ማስረጃዎችና ምስክሮች ይቀርቡበታል። ከስድስት ቀን የፍርድ ቤት ቆይታ በኋላ የፍርድ ውሳኔው በአስራ ሁለቱ የፍርድ ቤት ሸንጎ አባላት ውሳኔ ላይ ይወድቃል። ፍረዱም አስራ ሁለቱ ሸንጎዎች በሙሉ ድምፅ የሚያፀድቁት መሆን አለበት። ቀጥሎም ሸንጎዎቹ በማስረጃዎችና በአሳማኝ ምክንያቶች አየተከራከሩ ድምፅ እየሰጡ ለመወሰን ይቀመጣሉ። አስራ ሁለቱም በተለያዬ የስራ መስክ የተሰማሩ እና ጀተለያየ ማንነት ያላቸው ናቸው። አርክቴክት፤ ደላላ፤ የማስታወቂያ ባለሙያ ፤ ባንከር፤ ሽማግሌ፤ ዘረኛ፤ ኳስ ደጋፊ፤ ወዘተ አይነት ሰዎች ናቸው። በመጀመሪያም ወደ ድምፅ አሰጣጡ ይሸጋገራሉ አስራ አንዱ አሸንጎ አባላት የልጁን ወንጀለኛነት ሲያምኑ አንድ የሸንጎ አባል ደግሞ ልጁ ጥፋተኛ አይደለም ሲል የሸንጎው ክርክር ይጀምራል።

አስራ አንዱም የሸንጎ አባላ ብቻውን ድምፅ በሰጠው ሰው ላይ ተቃውሟቸውን ቢያሰሙም ሸንጎ ስምንት ግን አሳማኝ ማስረጃዎች እስካልተገኙ ድረስ በወጣቱ ላይ ጭፍን ፍርድ እንደማይሰጥ በአቋሙ ይፀናል። አስራ ሁለቱም ሸንጎዎች እንደተላበሱት ማንነት በወጣቱ የፍርድ ስርዓት ላይ እየተነሱ አመለካከታቸውን እና ውሳኔያቸውን ያራምዳሉ። እያንዳንዳቸው በጭፍን ጥላቻ፤ በዘረኝነት፤ በምስክሮች ጭፍን አመኔታ፤ በምክንያታዊነት፤ በጥልቅ አሳቢነት ክርክራቸውን ይቀጥላሉ። ሸንጎ ስምንት ግን ሁሉም ለሚያቀርቡት ማስረጃ ጥያቄዎችና አሳማኝ መልሶችን እየመለሰ የወጣቱ ወንጀለኛነት ላይ እንዲጠራጠሩ ያደርጋቸዋል። በሂደት አንዳንድ የሸንጎ አባላት በአሳማኝ ማስረጃዎችና በሌሎች የሸንጎ አባላት መጥፎ ግፊት ወደ ሸንጎ ስምንት ሀሳብ ይቀላቀላሉ። በዚህም ሂደት በወንጀሉ ላይ የቀረቡ ማስረጃዎች አጠራጣሪነታቸው እየጎላ ይሄዳል።አቋማቸውን ለመቀየር ከዘገዩት መሀል ሸንጎ አስር አንዱ ሲሆን በወጣት ማህበረሰብ፤ የአኗኗር ደረጃ ላይ ተንተርሶ በዘረኝነት ይቃወማል። በዋናነት ግን ሸንጎ ሶስት እስከ ተውኔቱ መጨረሻ ድረስ ብቻውን የወጣቱን ወንጀለኛነት በጭፍን ጥላቻ እና በቁጣዎች ታጅቦ የሚቀጥል ሰው ነው።

በተውኔቱ መጀመሪያ አካባቢ ወደ ሸንጎ ስምንት ውሳኔ ወይም ደግሞ የልጁን ወንጀለኛ አለመሆን ያመነው ስደተኛ ሽማግሌ ሸንጎ አስራ አንድ ነበር። የዚህም ምክንያት ሸንጎ አስር በወጣቱ ላይ በዘረኝነት ስለወሰነ ነበር። በመቀጠልም ሸንጎ አምስት ምርጫውን ይቀይራል። እሱም ከሸንጎ አስር የሚነሳው የዘረኝነት ወሳኔ ነበር ሀሳቡን ያስቀየረው። ምክንያቱም ከተከሳሹ ጋር ተመሳሳይነት ባለው የኑሮ ደረጃ ስላደገ ነበር። በመቀጠልም የተለያዩ ማስረጃዎች እና የምስክሮች የተሳሳተ ምስክርነት በሸንጎዎቹ እየተመረመሩ የሸንጎ አባላት ድምፃቸውን እየቀየሩ ይሄዳሉ። በመሀል ሸንጎ ሁለት፤ አምስትና ስድስት ወጣቱ ጥፋተኛ አይደለም የሚለውን አቋማቸውን ይቀይራሉ።ክርክሩም ይቀጥልና የተከሳሹ ጥፋተኛ አለመሆን እየጎላ ይሄዳል። በቀጣይ በሚሰጡት ድምፅም ዘጠኝ የሸንጎ አባላት ጥፋተኛ አይደለም ሲሉ ሶስቱ ደግሞ ጥፋተኛ ነው ብለው ክርክሩ ይቀጥላል። በመጨረሻም ሸንጎ ሶስት ብቻ በጭፍን ጥላቻው ግትርነት ምክንያት ብቻው የቀራል። ሁሉም የሸንጎ አባላት ብቻውን እንደሆነና ምንም አሳማኝ ማስረጃ ማምጣት እንዳልቻለ ይነግሩትና ፍርዱ በልጁ ጥፋተኛ አለመሆን ይጠናቀቃል።

### 3.2 አስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር

አስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት የአንድ ወጣት የፍትህ እጣ ፈንታ በአስራ ሁለት የሸንጎ አባላት ውሳኔ ላይ ሲወድቅ ያሳየናል። በተውኔቱም የአስራ ሁለት የሸንጎ አባላት የተለያዩ ማንነት ውስጥ የፍትህ ስርዓት ሲዛባ ይታያል። የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ የሚያተኩረው ዘር ወይም ዘረኝነት በተለዋዋጭ ሀይሎች በፍትህና በዳኝነት ውስጥ ያለውን አድሎ ማጥናት ነው። 12ቱ እንግዶች ተውኔትም የዘር ሂሳዊ ፅንሰ አሳብ ከሚያነሳቸው ጥያቄዎች አንፃር እንደሚከተለው ተተንትኗል፦

#### 3.2.1 የገፀ-ባህሪያት አሳሳል ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር

ከላይ እንደተገለፀው በዚህ ተውኔት የዘረኝነት ሰላባዎች በገፀ ባህሪያት እንጅ በስርዓቶች ላይ አይደለም የሚንፀባረቀው።ማለትም በተውኔቱ የዘረኝነትን አስከፊነት ለመግለፅ የገፀባህሪያትንን አመለካከት ላይ ትኩረት ተደርጓል። አንዳንድ የሸንጎ አባላት ተከሳሹ ከመጣበት ማህበረሰብ አንፃር ወንጀሉን በቀላል እንደፈፀመው ይከራከራሉ። በዋናነት ግን በሸንጎ አስር ላይ የሚደጋገም የዘረኝነት ፍረድ ይንፀባረቃል።

**ሸንጎ አስር(ዘረኛው)፡-**

በጣም ግልፅ የሆነ የዘረኝነት አመለካከት ያለው የሸንጎ አባል ነው። ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ማህበረሰቦች የሚዎጡ ሰዎች በተፈጥሯቸውህቀኝነት የጎደላቸው ወንጀለኞች እንደሆኑ ጭፍን ጥላቻ ባለው ስሜት ይከራከራል።

> *"አስር፣ ከንደዚህ አይነት ሰፈር የሚወጡ ሰዎች ምን አይነት አረመኔ ሰዎች እንደሆኑ ብቻ አይ ....መቼም ታውቃቸዋለህ (መሀረብ አውቶ ይናፈጣል፡፡)"(ገፅ 10)*
>
> *"አስር፣ በነገራችን ለይ እውነቱን ለመለየት ከባድ ነገር አይመስለኝም ፡፡ ኢደለም እንዴ ? ልጅ አባቱን ገድሏል ፡፡ በቃ እውነቱ ይህ ነው ፡፡ አውነት መሆኑን ለማወቅ ጉዳዩ ልጅ ያደገበትን ሰፈር ማየት በቂ ነው፡፡"(ገፅ 11)*
>
> *"አስር፤(በቁጣ) ብሩህ ? ብልህ ልጅ ነው ያልከው፣ከደንቆሮዎቸ አንዱ ነው ፡፡ብሩህ ጥሩ አማርኛ እንኳን እንኳን በአግባባ መናገር የማይችል ተራ ልጅ ነው"(ገፅ 10)*

ይህም ገፀ ባህሪ ካለበት የዘረኝነትና ጭፍን ጥላቻ መህል በመጨረሻም የሸኅጎ ስምንት ምክንያታዊ ጥልቅ አሳቢነት አስተሳሰቡን ይቀይረዋል።ደራሲው ጭፍን ጥላቻዎችን፤ የዘረኝነት አስተሳሰቦችን በሙሉ ሞራላዊ ጥያቄዎችና ጥልቅ አስተሳሰብ እንዴት የሰዎችን አመለካከት እንደሚቀይሩ የገለፀበት መንገድ ይደነቃል።

***ሸንጎ አምስት (ወጣቱ)፡-***

ይህ ገፀ ባህሪ ያደገበትና የተወለደበት ማህበረሰብ ከተከሳሹ ጋር በመመሳሰሉ ከሸንጎ አስር ለሚመጡ የዘረኝነት ትንኮሳዎች ተፅዕኖ ፈጥሮበት ውሳኔውን በማስቀየር የተከሳሹን ወንጀለኛ አለመሆን እንዲመርጥ ያደርገዋል።

> *"አስር፣በፊትም እኮ ተናግሪያለው፣እነዚህ ሰዎች ከባድ እና አስቸጋሪ ናቸው፡፡እነሱን ማመንም ማየትም አልፈልግም (ለትንሽ ደቂቂ ዝምታ ይሆናል፣አምስት መናገር ይጀምራል)*
>
> *አም ስት፣ ህይወቴን በሙሉ አሁን በምትሉት ሰፈር ውስጥ ነው ያሳለፍኩት*
>
> *አስር፣ ምንድን ነው የሰማውት*
>
> *አምስት፣ አዎ በቆሻሻ የተሞሉ ሜዳዎች ለይ ነው እየተጫትኩ ያደኩት፡፡ ...አሁን ድረስ ሽታዎቹ ይሰሙኛል...*
>
> *ፎርማን፣ ሄይ.. ምክንያታዊ እንሁን ፣ነገሮችን ሁሉ ግለሰባዊ ማድረገር የለብንም*
>
> *አምስት፣(ከተቀመጠበት ይነሳል ፡፡ እጁን ጠረጴዛው ለይ ያኖራል፡፡ ) በቀጥታ አንተን የሚመለከት ነገር ሲወራ ለምንድን ነው ግለሰባዊ ማታደርገው ? (ሁሉንም ያያቸዋል ፡፡ ኢያዩት ነው፣እንደተቆጣ አፍጦ ያያቸው እና ይቀመጣል፡፡)"(ገፅ 18)*

ደራሲው በገፀባህሪው ውስጥ በመጠኑም ቢሆን ዘረኝነት በተቋማት ውስጥ በሚገኙ ሰራተኞች የዘር ልዩነት እና ተቋማቱ በራሳቸው ዘረኝነትን መሰረት ያደረጉበት ጉዳይ የተቋሙን አባላት ጭምር እንዴት ተፅዕኖ ውስጥ እንደሚያስገባቸው ይነግረናል።

***ሸንጎ አስራ አንድ (ስደተኛው)፡-***

ይህ ገፀባህርይ የዘር ውክልነት ባይሰጠውም መጤ እንደሆነ ተደርጎ በሸንጎ አባልነት የተካተተ ገፀባህርይ ነው። በዚህ ገፀ ባህሪ የዘረኝነት ጥቃቶችን በማካተት ለሚነሱ ሞራላዊ ጥያቄዎች በዘረኝነት መገፋቱ ወደ ፍትሀዊነት ሲመራው ይታያል። በሸንጎ ሰባት የደረሰበትን የዘረኝነት ንግግር ስንመለከት፡-

*"ሰባት፣(በቁጣ)ምን ማለት ነው ..አልገባህም ማለት ምን ማለት ነው፣? እኔን እንዲህ ለመናገር የሚያስችልህ ምን ያለህ ይመስልሀል፣ማን ስለሆንክ ነው(ለሁሉም) ይሄን ሰውዩ እንዴት ነው የወደዳችሁት፣ ትናንትና ሀይወቱን ለማትረፍ ፈርጥጦ መትጦ ሲያበቃ እዚህ የምናካሂደውን ስርዐት እንዴት ማካሄድ እንዳለብን ሚመክረን ፣ምን አይነት ክፍት አፍነት ነው*

*አስረ አንድ ፣ ስደተኛ ነህ እያልከኝ ነው*

*ሰባት፣ በደንበ ነዋ መጤ ነህ በሀገሬ መተህ አፍህን ልትከፍትብኝ ትፈልጋለህ*

*አራት፣ ማንም እዚህ ያለን ሰዎች ከየት መምጣታችንን መጠየቅ የለበትም*

*ሰባት፣እኔ እዚህቹ ጋር ነው የተወለድኩት...እዛች ጋር*

*አራት፣ኣባትህስ ከየት ነው የመጣው(ወደ ውጭ የሚያየውን ሰባትን እያየ)"(ገፅ 42-43)*

በዚህ ቃለ ተውኔት ውስጥ ደራሲው በሸንጎ አራት ጥያቄያዊ ቃለ ተውኔት የገለፀው የዘረኝነት ሞራላዊ ጥያቄ የሚደነቅ ነው። ዘረኝነት በሰው ልጆች ውልደት ውስጥ ባሉ ጉዳዬች ላይ የሰው ዘር አንድነትንና የሰው ዘርን ወደ ምድር መጤነትን ያስተላለፈበት መንገድ ቀላል ጥያቄ አድርጎ በተመልካቾች ላይ ጥልቅ ማሰላሰል ይፈጥራል። በአጠቃላይ በተውኔቱ ዘረኝነትን እንዲያንፀባርቁ የተደረጉት ገፀባሕርያት እነዚህ ናቸው።

## 3.2.2 የስርዓቶች ወይም ተቋማዊ የዘረኝነት ምርመራ

የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ ዘረኝነት በህጎችና በተቋማት ውስጥ የሚያተኩር እንጅ በግለሰቦች አስተሳሰብ ላይ ብቻ እንዳልሆነ ይገልፃል። በዚህ ተውኔት ምክንያታዊነትንና ከዘረኝነት የነፃ ማንነትን የሚሸከምና የአስራ አንድ የሸንጎ አባላትን አመለካከት የሚያስቀይር ሸንጎ ስምንት(አርክቴክቱ) ገፀባህርይ ነው። ተውኔቱ በገፀ ባህሪያቱ ስለ ዘረኝነት ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ የሞራል እሳቤዎች አንፃር የፍርድ ስርዓት ላይ ትኩረት ያደርጋል። ይህም ፍትህን በስርዓቱ ወይም በተቋሙ ከዘረኝነት የነፃ ለውጥ ከመፍጠር ይልቅ በግለሰቦች የግል ጥላቻ ላይ ማድረጉ ከዘር ሂሰዊ ፅንሰ ሀሳብ መሰረታዊ ምርመራ አንፃር ደካማ ጎኑ ያደርገዋል። ምክንያቱም የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ በዋናነት የአሰራሮችን፤ የመርሆችን ብሎም የደንቦችን የዘረኝነት ተፅዕኖ ላይ ስለሚያተኩር ነው።ሆኖም ዘረኝነት በተቋማት ውስጥ በሚገኙት ግለሰቦች አመለካከት፤ ህጎችና ፍትሀዊነት ላይ ያለውን ተፅዕኖ ደራሲው በገፀባህሪቱ የገለፀበት መንገድ ሊደነቅ ይገባል።

## 3.2.3 የተለያዩ ውክልናዎች

የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ ፍትሀዊ ስርዓቶችን ለማካሄድ የሸንጎ አባላቶቹ የማህበረሰቡን የዘር ልዩነት ማንፀባረቅ አለባቸው ወይም የተለያዩ የዘር ውክልናዎችን መላበስ አለባቸው ብሎ ያምናል። በዚህ ተውኔት ውስጥ የሚገኙት አስራ ሁለት የሸንጎ አባላት መካከል ከሸንጎ አስር፤ አስራ አንድ እና አምስት ውጭ የሌሎቹ ገፀባህሪያት በሚገባ የዘር ልዩነት አለመኖር ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ደካማ ጎኑ ያደርገዋል።

## 3.2.4 የተከሳሹ አመለካከት

በተውኔት መጀመሪያ በዋናው ዳኛ ስለ ተከሳሹ ለሸንጎ አባላት ተነግሯቸዋል። እንዲሁም የፍርድ ቤት የምስክሮችና የተከሳሹን ንግግር ሰምተዋል። ነገር ግን በተውኔቱ ውስጥ አልፎ አልፎ ከገፀባህሪያት ስለጨተከሳሹ ቢነጠርም የተከሳሹ አመለካከት ከእራሱ አንደበት አይሰማም። የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ ይሄን አካሄድ ብዙ ጊዜ የተገለሉ ድምፆችንስለሚታፈኑ ይተቸዋል። ተውኔቱ ላይ ተከሳሹን ከህግ ስርዐቱ ጋር ያለውን የግል አመለካከት ለመተንተን አመቺ አያደርገውም።

## 3.2.5 ተውኔቱ ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ለማህበረሰቡ ያለው ጠቀሜታ

ዘረኝነት በተለያዩ ማህበረሰቦች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በጣም ተፅዕኖ የሚያሳድር፤ ግጭት የሚፈጥር ብሎም በሰው ልጆች ህይወት መጥፋት ምክንያት እየሆነ የመጣ ጉዳይ ነው። አስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔትም ይህን አስከፊ አስተሳሰብ በፍርድ ስርዓት ላይ እንዴት ተፅዕኖ እንዳለው አሳይቷል። በእርግጥም በተውኔቱ ስርዐታዊ ወይም ተቋማዊ ህግጋትና ደንቦች ላይ ዘረኝነት ያለው አስከፊነት በሚገባ ባይገለፅም በገፀባህሪያት ግለሰባዊ የዘረኝነት አመለካከት ህጎችና ደንቦች ላይ እንዲሁም

ፍትህ እንዴት እንደሚጓደል ያሳያል። ለማህበረሰቡም ያለው ጠቀሜታ እንደ ፍርድ ፍትህዊነት የህግ ባለሙያዎች ከዘረኝነት የነፃ ስርዓት እንዲያካሂዱ እና እንደ ግለሰብ ደግሞ እራሱ ማህበረሰቡ የዘረኝነትን ከፋት እንዴት ከእውነት እንደሚርቅ ተውኔቱ ያስገነዝባል።

## 3.3 አስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት ከሞራላዊ ሂስ አንፃር

አስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት ጥልቅ የሆነ የሞራል ጥያቄዎችንና እሳቤዎችን የያዘ ተውኔት ነው። ተውኔቱ በማህበረሰብ ይበልጥ ደግሞ በግለሰቦች የሞራል ማንነት ተፅዕኖ ውስጥ ይሽከረከራል። በዚህ ተውኔት በሚገኙት አስራ ሁለት የፍርድ ሸንጎ ገፀ ባህሪያት የግለሰብ ሞራልንና የተለያዩ ማህበረሰቡን የሚወክሉ እሴቶች ይንፀባረቃሉ። ሞራላዊ እሴት በሰፊው ከሚንፀባረቅባቸው መንገዶች ፍትህ አንዱ ነው። በፍትህ ስርዓት ውስጥ ግለሰቦች ቡድን ሲሆኑ ሞራላቸው ፍትህ ለሚሻው አካል ላይ እንዴት ሚዛን እንደሚደፋ ተውኔቱ በሚገባ ያሳያል። አጥኚው ይህን ተውኔት ሞራላዊ ሂስ ከሚያነሳቸው ጥያቄዎች አንፃር እንደሚከተለው ይተነትናል፦

### 3.3.1 በተውኔቱ ውስጥ ያሉት ገፀባሕርያት በሞራላዊነት እንዴት ተስለዋል?

በአስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት እያንዳንዱ የሸንጎ አባል በክርክር ሂደት ውስጥ የተለያዩ የሞራል አቋሞች፣ አመለካከቶች፣ የታማኝነት ደረጃዎችን ያሳያሉ። በዚህም ሞራላቸው የሚያሳየው ፍትህ፣ አድሏዊነትን፣ ሀላፊነት፣ ተጠያቂነት ወ.ዘ.ተ ከማንነታቸው አንፃር እንዴት እንደሚወጡ ነው። ቀጥሎም ገፀባህሪያቶቹ ከሞራላዊነት አንፃር እንዴት እንደተሳሉ ይተነተናል።

***ሀ. ፎርማን(አጋፋሪ)፦*** ይህ ገፀባህርይ ፍትህዊ ለመሆን ይሞክራል። ነገርግን ከሞራላዊ ክርክሮች ጋር በጥልቀት እየተሳተፈ ችግሮችን ከመፍታት ይልቅ በተሰጠው ሀላፊነት የሸንጎ አባላቱን ለመቆጣጠር ይሞክራል። ቡድኑን የመምራት ሀላፊነቱ ደስተኛ ስላደረገው የተከሳሹ ፍትህ ወደ ጎን በመተው የሸንጎዎችን ስርዓት በማስፈጸም የተጠመደ ሰው ነው። ቢሆንም በመጀመሪያ የወጣቱን ጥፋተኝነት ምርጫቸው ካደረጉ ሸንጎዎች መካከል አንዱ ነው። አልፎ አልፎም በሚጠይቃቸው ጥያቄዎችና በሚሰጣቸው መልሶች ምክንያታዊ ለመሆን ሲጥር ይታያል።

*"**ፎርማን፣** ሄይ.. ምክንያታዊ እንሁን ፣ነገሮችን ሁሉ ግለሰባዊ ማድረገር የለብንም"(ገፅ 18)*

**ለ. ሸንጎ ሁለት(ባንከሩ)፦** የዋህና በውሳኔዎቹ እርግጠኛ ያልሆነ ሰው ነው። ብዙ ጊዜ ከሌሎቹ የሸንጎ አባላት ስድብና የማንቋሸሽ ጥቃት የሚደርስበት በራስ መተማመን የሌለው ገፀባህርይ ነው። ለእራሱ ከለላ በሰጠለት ሰው ሀሳብ የሚመራ ፈሪ አይነት ሰው ነው። በተውኔቱ መጀመሪያ እንደ አብዛኛዎቹ የሸንጎ አባላት የወጣቱን ጥፋተኝነት ያምናል።

> *"**ሁለት፣** (ደነገጥ....ብሎ) እ...እ... (ረጅም ፖዝ) ያው... እኔ ወንጀለኛ ነው የምለው....ያው እንደተባለው .....ያው....ያው ግልፅ ነው " (ገፅ 15)*

ቆይቶም በክርክሮች በማመን የተከሳሹን ጥፋተኛ አለመሆን ያምናል። መልሶ ደግሞ ተከሳሹ ላይጥፋተኛ ብሎ ድምፁን ሲሰጥ በስነልቦና ስሙ ዘ ሞንቴ ሃል ዲሌማ የተሰኘው ጥናት ሀሳብ የሰው ልጆች የምርጫ ችግር በዚህ ገፀባህርይ ሞራል ላይ ተፅዕኖ ሲፈጥር ይታያል።

> *"**ሁለት፣**መቼም በጣም የሚያሰገርሙ የፍርድ ታሪኮች ሰምተህ ታውቃለህ፡፡ እንዳንድ ምስኪን ሰዎች ይፈረድባቸው እና ከሆነ አመት በኋላ በስህትት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ እኔም ከአመታት በፊት ወንጀለኛ ነው ብየ አምንበት ሀሳቤን ቀየርኩና ልጁ ከተፈታ ከአመታት በኋላ ወንጀለኛ እንደሆነ ተደረሰበት።"(ገፅ25)*

ጥናቱ ሰዎች በምርጫ አጣብቂ ውስጥ ሆነው አንድን ነገር ከመረጡ በኋላ ምርጫቸውን ቀይረው ያ የቀየሩት ምርጫ ልክ እንደነበር አውቀው ከሚሰማቸው ፀፀት፣ መጀመሪያውኑ በአቋማቸው ቀጥለው ምርጫቸው ስህተት ቢሆን ከሚሰማቸው ፀፀት ከፍተኛ ነው ይላል። በዚህም ገፀባህርይ ሞራልዊ የፍትህ ምርጫ ላይ ደራሲው ያስገነዘበው የስነልቦና ተፅእኖ የሚደነቅ ነው።

**ሐ. ሸንጎ ሶስት(የጠፋው ልጅ አባት)**፦ በተውኔቱ የተለያዩ የሞራል ብልሹነት ያላቸው ገፀ ባህሪያት ቢኖሩም ይህ የሸንጎ አባል ግን እስከ ተውኔቱ መጨረሻ ድረስ የሞራል ውድቀት የሚታይበት ሰው ነው። ግትር፣ እያንዳንዱን ሀሳቦቹንእና

እንቅስቃሴዎቹ በቁጣና በግልፍተኝነት እንጅ በምክንያታዊነትና በቅንነት ፍትህን የሚያሰፍን ሰው አይደለም። ከምንም አይነት ክርክርና የማስረጃዎች ምርመራ እንዲሁም የድምፅ አሰጣጥ በፊት ይህ ገፀባህርይ በተከሳሹን ጥፋተኝነት በጭፍን ጥላቻ ያምን ነበር።

*"**ሶስት**፣ ከዛም ወልዶ ያሳደገውን አባቱን ደረቱን ወግቶ የገደለው አረመኔ ልጁ ላይ እስከ ህይወት መጨረሻ ይቆሉፉበታል (ሃሃሀ) በዚህ እስማማለው"(ገፅ 8)*

የዚህ ገፀባህርይ የሞራል ብልሹንት ምክንያት የሆነው ያለፈው ህይወቱ ጠባሳ ነው። ሰውየው ወጣልት ልጁ ከአመታት በፊት ጥፋት ሰርቶ ጠፍቶበታል። በፍርዱም ወቅት ተከሳሹን ልክ እንደጠፋው ልጁ በመመልከት እስከ ተውኔቱ መጨረሻ ድረስ በጭፍን ጥላቻ ይጓዛል።

*"**ሶስት**፣ አንድ ልጅ አለኝ፣, (ፖዝ) አንድ ልጅ አለኝ ...የዚህ ዘመን ልጆች አይሰሙህም፡፡(ፐዝ ፤ሃሳብ) ስምንት አመት እያለ አንድ ቀን ጠብ ውስጥ አየሁት ፡፡ መጣላቱ አልነበርም ያናዳደኝ ...ሲሸሽ አየሁት አፈርኩ ፤ ጠራውት እና አንድ ነገር ነገርኩት፣ወንድ እንዲሆን፣ሲሸሽ ባየው አፈርድሜ እንደማስግጠው ነገርኩት፣አለፈ አስራ አምስት አመት ሆነው፣አደገ ጎረመሰ፣ልመከረው ብነሳ ምን እንዳደረገ ታውቃላችሁ? በጥፊ መቶኝ ሄደ....(ዝምታ) በጥፊ መቶኝ ሄደ ....ካየውት ሶስት አመት ሆነኝ....ዋልጌ ልጅ አልወድም፡፡ .....ለምን እንደምትመክራቸው፤ ተው እንደምትላቸው አይገባቸውም...(ዝምታ) አዎ ስለ ፍቅር ብለሀ ባደረከው ተቃራኒ ምላሽ ሰተው ቅስምህን ይሰብሩታል ....በናፍቆት እና እና ብቸኝነት ይቀጡሀል.......(ዝምታ) እሺ ወደ ስራችን እንሂድ(ይነሳ እና ወደ መስኮት ጋር ሂዶ እያሰበ ያያቸዋል)"(ገፅ 18")*

በተጨማሪም ከአንዳንድ የሸንጎ አባላት ጋር ክርክሮችን ወደ ፀብ በመውሰድ ለዱላ ሲጋበዝ ይታያል። ይህም ገፀባህርይ የግለሰብንና የቤተሰብ ተፅዕኖ ከሞራላዊ አመለካከቶች ጋር በማዋሀድ ከተውኔቱ ጋር ይራመዳል።

***መ.* ሸንጎ *አራት* (ደላላው)፦** ይህ ገፀባህርይ ምክንያታዊ ሰው ነው። እራሱን ከሌሎች የተሻለ ምክንያታዊ እንደሆነ አድርጎ ቢያስብም ሌሎች የሸንጎ አባላት ከክርክር ርዕስ ሲወጡ የአጋፋሪውን ድርሻ በመውሰድ ሀላፊነት ሲወጣ ይታያል።በአባላቱ የተለያዩ ሀሳቦች ሲንፀባረቁ ይጠይቃል። ቢሆንም ግን ለአንዳንድ ማስረጃዎች በመጠኑም ግትርነት ይታይበታል። በተውኔቱ መጀመሪያ አካባቢ ላይ ይህ ቃለ ተውኔት ይገኛል።

*"**አራት**፣ ምንድን ነው ጎበዝ እኛ እኮ ትልልቅ ሰዎች ነን እንደ ህፃናት አንሁን፣*

*እንደማማጥ፣በሰከነ እና በተረጋጋ መንፈስ እንደ አዋቂ እናውራ"(ገፅ 14)*

*በዚህ ገፀ ባህሪ አንድ ደራሲው የሚደነቅበት አስተሳሰብ ተንፀባርቋል።*

*"**አራት**፣ ጎበዝ በጣም ሙቀት እና ወበቅ ነው ፡፡ ይሄ ደግሞ ቁጡ ሊያደርገን ይችላል፡፡ማለቴ ባህሪያችንን ትንሽ ሊቀይረው ይችላል፡፡"(ገፅ 8)*

በዚህም ቃለ ተውኔት እንዲሁም በተውኔቱ ደራሲው የሚናገረው ምቹ ያልሆነ ስፍራ፤ የአየር ሁኔታ ወይም ተፅዕኖ ያለበት ነባራዊ ስፍራ ላይ ያሉ ሰዎች እንዴት በስነልቦና ጫና ሞራላዊ ምላሻቸው እና ውሳኔዎቻቸው ተፅዕኖ ውስጥ እንደሚገባ ነው። ደራሲው ይሄን የስነልቦና አስተሳሰብ የገለፀበት መንገድ የሚደነቅ ነው።

**ሰ. ሸንጎ አምስት (ወጣቱ)፦** ይህ ገፀባህርይ በተውኔቱ ውስጥ ለሚቀርቡ ክርክሮች በድፍረት ምላሽ ባይሰጥም በተከሳሹ ላይ ለሚደርሱ ዘረኝነትን የተንተራሱ ሀሳቦች ጋር ይታገላል። በመጀመሪያ የተከሳሹን ጥፋተኝነት ከአመኑ አባላት መካከል አንዱ ነው። ቀጥሎ ግን የተከሳሹ ጥፋተኛ አይደለም እንዲል ሀሳብ ያስቀየረው ዘረኝነት ነበር። ማለትም ሸንጎ አስር የወጣቱን የኑሮ ደረጃ እና የመጣበትን ማህበረሰብ በመወከል ለሚያራምደው የዘረኝነት ውሳኔ ይህ ገፀባህርይ ከተከሳሹ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አስተዳደግ ስለነበረው ነበር ሀሳቡን የቀየረው። ይህም የሆነው የገፀባህሪው ሞራል በራሱ ፍትሀዊ ፍርድ ሳይሆን ግላዊ መገፋት ውስጥ ስለተያያዘ ነበር።

*__አም ስት__፣ ሀይወቴን በሙሉ አሁን በምትሉት ሰፈር ውስጥ ነው ያሳለፍኩት*

*__አስር__፣ ምንድን ነው የሰማውት*

***አምስት፣*** *አዎ በቆሻሻ የተሞሉ ሜዳዎች ላይ ነው እየተጫትኩ ያደኩት፡፡ ...አሁን ድረስ ሽታዎቹ ይሰሙኛል...(ገፅ 18)*

*"**አስር**(በቁጣ) ብሩህ ? ብልህ ልጅ ነው ያልከው፣ከደንቆሮዎች አንዱ ነው ፡፡ብሩህ ጥሩ አማርኛ እንኳን እንኳን በአግባባ መናገር የማይችል ተራ ልጅ ነው*

***አስራ አንድ****(በቀስታ እና በለበጣ ) ጥሩ አማርኛ እንኳን አያወራም ?*

***አራት፣*** *በርግጥ ልጁ ብልህ/ ጮሌ ነው(አራት እያወራ አስር ተነስቶ አስራ አንድን ሲያይ ይታያል፡፡ በመሀለ ዝምታ ይሆናል፡፡አስር ሲቀመጥ አምስት ሲነሳና ዙሪያውን ነርቨስ እንደሆነ ሲመለከት ይታያል፡፡)*

***አምስት፣*** *ምርጫዩን መቀየር እፈልጋለው ወጣቱ ጥፋተኛ አይደለም(ሶስት ያጨብጭባል ፡፡ከዛም ወደ መስኮቱ ጋር ይሄድና ደግሞ ያጨበጭባል)"(ገፅ 31)*

ለውሳኔዎቹ ክርክሮችንና ማስረጃዎችን መረዳት ውስጥ የዚህ ገፀባህርይ ግራ መጋባት የሚታየው በተውኔቱ መጨረሻ አካባቢ ምርጫውን ቀይሮ በስተመጨረሻ ደግሞ የልጁን ጥፋተኛ አለመሆን ሲያምን ነው። ደራሲውም በዚህ ገፀባህርይ የሚያስተላልፈው ሞራላዊ እሳቤዎች እና ምላሾች በግል ህይወት ያለፉ ጠባሳዎች መሀል የራሳቸውን ተፅዕኖ እንደሚፈጥሩ ነው።

***ረ. ሸንጎ ስድስት(ሰዓሊው)፡-*** *ይህ ገፀባህርይ ደግሞ በሸንጎዎች መሀል ለሚነሱ ክርክሮች በጭልቀት የማይተነትን፤ ከሸንጎ አባልነት ይልቅ ታዛቢ የሚመስል ሰው ነው። ነገር ግን ሀሳቡንም ምርጫውንም በድፍረት ይናገራል። ከሞራላዊነቱ አንፃር ለመተንተን የግድ አንድን አስተሳሰብ ወይም ሞራላዊ ጉዳይ ይዞ መገኘት አለበት። ይህ ሰው በተውኔቱ መጀመሪያ የወጣቱን ጥፋተኛነት አምኖ ቢቀበልም በኋላ በምክንያቶች በማመን ሀሳቡን የቀየረ ሰው ነው።*

***ሸ. ሸንጎ ሰባት( ኳስ ደጋፊ )፡-*** *በሞራላዊነት ደካማ ተደርጎ የተሳለ ገፀባህርይ ነው። የእግር ኳስ ደጋፊ በመሆኑ የሸንጎው ፍርድ ላይ የውድድር ሰዓት እንዳይረፍድበት ሲል ለክርክሮችና ለማስረጃዎች ግድ የሌለው እና በምርጫ አሰጣጡ ላይ ደካማ ሰው ነው።*

*""**ሰባት፤** እውነት ነው እንቀመጥ ፡፡ጉዳዩን ቶሎ እንየው፡፡ መፍጠን አለብን ፡፡ በነገራችን ላይ ትኬት ቆርጨያለወ የዛሬ ማታ ደርቢ ጫወታ ነው፡፡ ...የተከበሩ እባክዎትን ጉዳዩን ቢያሰጀምሩት፡፤"(ገፅ 10)*

ከተከሳሹ ፍትህዊ ፍርድ ይልቅ ምርጫውን በተሎ መጨረሱ ላይ ትኩረቱን ያደረገ እና በትንሽ ነገር የሚናደድ እና በትንሽ ነገር የሚደሰት ሰው እንደመሆኑ በክርክሩ ወቅት ለሚሰነዘሩ ሀሳቦች በግምትና በስሜታዊነት የሚናገር ሰው ነው። መጀመሪያ በተከሳሹ ጥፋተኝነት አምኖ በመጨረሻ ድምፆች ወዳዘነበሉበት የሸንጎ ስምንት ምርጫ ይቀላቀላል።

*"**ሰባት**፤አንድ ነገር ልንገርህ ይሄ ልጅ ወንጀሉን በትክክል ፈፅሟል ፡፡ መቶ አመት ብታወራኝ ይህንን አቋሜን ልታስቀይረኝ አትችልም "*

***ቀ. ሸንጎ ስምንት(አርክቴክቱ)፡-*** ይህ ገፀባህርይ የመልካም ሞራል ማዕከል ነው። በወንጀሉ ጉዳዮች ላይ በጥልቀትና በማስተዋል ለውይይት ሌሎችን የሸንጎ አባላት ጨምሮ የሚጋብዝ ሰው ነው። የሰዋዊ ርህራሄ ከትክክለኛ ፍትህ ጋር ተጣምሮ በጥልቅ አሳቢነትና በእርጋታ ተውኔቱን የሚሸከም ገፀባህርይ ነው። በምክንያታዊነት እና በማስተዋል እነትን ማግኘት እንደሚቻል የሚገልፅ የሸንጎ አባል ነው።

*"**ስምንት** እንድናወራበት ፤ ከመወሰናችን በፊት በጉዳዩ ላይ እናውራበት ነው እያልኩ ያለውት ፡፡ይሄ ልጅ እኮ ይህችን አስራ ምናምን አመት እንኳን ተረጋግቶ መኖር የቻለ ልጅ አይደለም፣ እናቱን በዘጠኝ አመት ያጣ ልጅ ፣ መጠን ከፍ ያለ እና ስር የሰደደ ችግር ያለበት ሰፈር ውስጥ ያደገ ቁጡ ተናዳጅ ልጅ፣ ፡፡እንደዚህ አይነት ችግር የበዛት ውስጥ ያደጉ ልጆችን የምናይበት መንገድ እኮ ትክክል አይደለም ፡፡፣ህይወት ማቆየት በራሱ ከባድ ነው፣ ከዛ ማህበረሰ ውጭ ያሉ ሰዎች የሚሠጣቸው የተሳሳተ ግምት ደግሞ ነገሩን ያብሰዋል፡፡ ኑሮው እና የመጣበት ሰፈርን መሰረት አድርጎ ወንጀለኛ ነው ብሎ መደምደም አግባባ ያለው አይመስለኝም "(ገፅ 13)*

በዚህ ቃለ ተውኔት ውስጥ ሰዎችን በጭፍን ጥላቻና በቂ ባልሆነ መረጃ እንዲሁም በአኗኗር ደረጃቸው ወይም የመጡበትን ማህበረሰብ በመወከል ፍትህዊ ፍርድ እንደማይገኝ ተውኔቱ በዚህ ገፀባህርይ ይነግረናል። ከመጀመሪያው ጀምሮ የልጁን ጥፋተኝነት ባለማመን ብቻውን ይቆምና እስከ ተውኔቱ መጨረሻ ድረስ የአስራ አንዱን የሸንጎ አባላት ሀሳብ በምክንያታዊነት የሚያስቀይር ጥሩ ገፀባህርይ ነው።

**በ. ሸንጎ ዘጠኝ(ሽማግሌው)፡-** ይህ ገፀባህርይ ከሁሉም ገፀባሕርያት በእድሜ የገፋ እና በጣም የተረጋጋ ስብዕና ያለው ሽማግሌ ነው። ያመነበትን ነገር ከመናገር ወደኋላ የማይልና በረጅ የህይወት ልምድ ያካበተው የሞራል እሴት ከሸንጎ ስምንት ገፀባህርይ ጋር ያራምዳል። ደራሲው በዚህ ገፀባህርይ አንድ የሞራል ሀሳብ ያስተላልፋል። እድሚያቸው የገፋ እና የኑሮ ደረጃቸው ዝቅ ያሉ ሰዎች ሞራል ምን እንደሚመስል ከስነ ልቦናቸው አንፃር በዚህ ገፀባህርይ ያንፀባርቃል። በታሪኩ ውስጥ በተከሳሹ ላይ በሀሰት ከመሰከሩ ሁለት ሰዎች አንዱ ሽማግሌ እና ደሀ ሰው ነው። የዚህም ሽማግሌ የመገፋትና የመጣል ስነ ልቦና ውስጥ ደራሲው የሚነግረን የሞራል ጉድለት ብዙ የገህዱን አለም ሰዎች ይወክላል። ደራሲውም በዚህ የሞራል እሳቤ የሚደነቅ የታሪክና የገፀባህሪ ውህደትን አንፀባርቆበታል።

> *"**ዘጠኝ**፤(ከዝምታ በኋላ) ሰውየውን ለረጅም ግዜ በአትኩሮት ተመልክቼዋለው፡፡ከላይ ያደረገው ሰፊ ጃኬት ከብብቱ እስከ ጣቶቹ ለሁለት ተሰንጥቋል፤፤አስተውላችኋል ? ሽማግሌ የተቀደደ እና ያረጀ ጃኬት ማድርጉ ሳያንስ ሁለት ከዘራ ይዟል(ተነስቶ ወደ ቀኝ መድርክ ሄዶ ወደ ግርግዳው እንደዞረ ሲያወራ ይታያል)እውነቴን ነው ምላችሁ እዚህ ውስጥ ካላችሁት ውስጥ እኔ በተሸለ መንገድ ሰውየውን አውቄዋለው፡፡በህይወቱ ምንም ማንም ሳይሆን የኖረ፤በፍርሀት እና ጠቃሚ ባለመሆን ስሜት ውስጥ ያለ ሰው ፤በአካባቢው ባሉ ሰዎች መኖሩ በአግባባ ለሰከንድ ታውቆ የማያውቅ፣ በበጎም ሆነ መጥፎ ጎን ጋዜጣ እና መፅሄት ለይ ስሙ ወቶ የማያውቅ ተላላ ሰው ታውቃላችሁ? ሰባ አምስት አመት ሙሉ የማንም እይታን ያልሳበ ሰው.፤በጣም የሚያሳዝን ታሪክ፤እንደዚህ አይነት ታሪክ ላለው ሰው ይህ ጥሩ የመታወቂያ የመጠየቂያ ፤የመደመጫ እና የመታወሻ መንገዱ ሲያገኝ ወደ ኋላ ሊል አይችልም፣ ይህ ለሱ ትልቅ ኢጋጣሚ ነው፡፡የመደመጥ ፤የመፈለግ ፤የመኖርን ማረጋገጫ መንገድ "(ገፅ 29)*

**ተ. ሸንጎ አስር(ዘረኛው)፡-** በዚህ ገፀባህርይ ውስጥ ደራሲው በሰው ልጅ የሞራል ማንነት ላይ ዘረኝነት ምን ያክል ተፅእኖ እንደሚፈጥር ያሳያል። ይህ ገፀባህርይ ባለሀብት፤ ቁጡ ለማንም ግድ የማይሰጠው፤ ከእራሱ ውጭ ሰው በአይኑ የማይሞላ፤ ተከሳሹን በመጣበት ማህበረሰብና የአኗኗር ደረጃ በመነሳት ወንጀሉን እንደፈፀመ የሚያምን ዘረኛ ገፀባህርይ ነው።

> *"**አስር**፤ ከንደዚህ አይነት ሰፈር የሚወጡ ሰዎች ምን አይነት አረመኔ ሰዎች እንደሆኑ ብቻ እይ ....መቼም ታውቃቸዋለህ (መሀረብ አውቶ ይናፈጣል፡፡)"(ገፅ 10)*

በዚህ ገፀባህርይ ላይ አሳማኝ ያልሆነ የሞራላዊ አሳሳል ጉድለት ይታያል። ገፀባህርይው ከተውኔቱ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ገፅ 49( የተውኔቱ መጨረሻ ገፅ 50) ድረስ በዘረኝነትና በቁጡ ባህሪው ምክንያቶችን ሲሸሽ እና በግብዝነት ሲከራከር ይቀያል። ለምሳሌ እስከ ገፅ 47 ድረስ በቂ ማስረጃዎች ከቀረቡ በኋላ እንዲህ ይላል፡-

> *"**አስር** ፤እናንተ ሰዎች ምን እያደረጋችሁ እንደሆነ አልገባኝም፡፡አብዳችኋል እንዴት ነው ይህንን ልጅ ንፁህ ነው ምትሉት፡፡እንደነዚህ አይነት ልጆች እንዴት እንደሚዋሹ እኔ ለናንተ አልነግራችሁም፡፡እውነት ምን ማለት እንደሆ አያውቁም፡፡ አንድ ነገር ልነገራችሁ( አምስት ተነስቶ ለአስር ጀርባው ሰቶ ወደ ግርግዳ በመሄድ ይቆማል) አዎ እንደዚህ አይነት ልጆች ሰው ለመግደል ምንም በቂ ምክንያት አይፈልጉም፡፡ መጠጥ ፤ስካር አሊያም ሀሺሽ ማጨስ በቂ ነው፡፡(ዘጠኝ ከተቀመጡበት ተነስተው ወደ መስኮቱ በመሄድ ወደ ውጭ ያያል) አዎ እነዚህ እኮ ጠጥተው በየ ቱቦ ስር ወደቀው የሚያድረሩ ሀላፊነት የማይሰማቸው ናቸው.............እዚህ ሰፈር ስላደጉ ሰዎች ባህሪ ታውቃላችሁ ? ምን ያህል ስነምግባር የሌላቸው እንደሆኑ ታውቃላችሁ ? እውነት እየነገርኳችሁ ነው፡፡(አራት ከአስር ፊት ይቆማል ፤አስር ዝም ይላል በቤቱ ዝምታ ይሰፍናል፡፡)" (ገፅ 47)*

*ቀጥሎም በገፅ 49 እንዲህ ይላል፡-*

> *"**አስር**፤ ሁሌ በጣም የምገረም ሰው ነኝ...ማንኛውንም ነገር ከመሰረቱ በማየተ የምናር ሰው ነኝ....አዎ ለፍርድ የማልቸኩል ግን ተጠራጣሪ ....ይህ ለዘማናት የያዝኩት ባህሪዩ ነው፡፡ሁሌ ወደ እውነት ለመቅረብ የምጥር ሰው፡፡ራሴን ወደ .....እ በዚህ ጉዳይ ግን ተሳስቼያለው አለመግደሉን የሚያሳይ ምክንያታዊ ጠርጣሬ አለ"(ገፅ 49)*

ደራሲው ይህን ያደረገበት ምክንያት በተውኔቱ ሁሉንም የሸንጎ አባላት በተለያዩ የሞራል ማንነቶች ላይ አላብሶ እንዳላበሳቸው ማንነት የየራሳቸው የፍርድ ምርጫ እየሰጠ ካስጓዛቸው በኋላ በመጨረሻ ወደ አንድ የፍትህ ውሳኔ ማድረስ

*ስላለበት ነው። በዚህም ምክንያት የሸንጎ አስር ምክንያታዊ ያልሆነ የሞራል ለውጥ እንዲፈጠር አድርጎታል። ይሄም የተውኔቱ አንዱ ደካማ ጎን ነው።*

***ቸ. ሸንጎ አስራ አንድ(ስደተኛው ሸማግሌ፡-*** *ይህ ሸማግሌ የሸንጎ አባል በጦርነት ምክንያት ወደዚች ከተማ የተሰደደ ሰው ነው። በተውኔቱም ጦርነትና መሰደድ የፈጠረበት ተፅዕኖ ሰበሞራላዊ እሳቤው ላይ ጎልቶ ይታያል። ሽማግሌው እረጋ ያለ እና ምክንያታዊ ለመሆን የሚጥር አይነት ሰው ነው። ይህም በጦርነት ማለፉ በጭቆና አስተዳደግ ማለፉ ትክክለኛ የሆነ ፍርድ እንዲካሄድ የሚገፋው ሽማግሌ ነው።*

*"**አስረ አንድ፣** እኔም እንደሱ ይሰማኛል፣ጎበዝ ትልቅ ሃላፊነት አለብን፣ይህ ጉዳይ ሰዎች ምክንያታዊ መሆንን እንዲያወቁ እና አንዲለምዱ ምክንያታዊንትን በማስፋፋት በማ ብራራት ትልቅ ሚናው አለው፡። ይህ የኛ ስራ ለዲሞክራሲ እድገት ወሳኝ ነው፡፡እውነቴን ነው ትልቅ ሀላፊነት አለብን ፡፡እኛ ሁላችን ....በ....ም ንድን ነበር ቃሎ...በኖቲፊኬሽን ...ማለትም በኢሜል ኢዚህ ቦታ እንደንመጣ ተደረገ፣ከመጣን በኋላም አንድ ከዚህ በፊት የማናውቀው ሰው ወንጀለኛ እና ንፅሁ መሆኑንን እንድናጣራ ሀላፊነት ተሰጠን፣ በምንሰጠው ፍርድ የምናገኘውም ሆነ የምናጣው አንዳች ነገር የለም፣ይህ አንዱ ጠንካራ እንደንሆን የሚያደርገን ምክንያት ነው፣በፍፁም ይሄን ጉዳይ ከራሳችን ግላዊ ጉዳይ ጋር ማገናኘት የለብንም"(ገፅ 37)*

በእርግጥም ይህ ገፀባህርይ በተውኔቱ መጀመሪያ የተከሳሹን ጥፋተኛነት ቢያምንም ቀስ በቀስ ግን በሸንጎ ስምንት የክርክር ሀሳብና አሳማኝ እውነተኛ ማስረጃ ፍለጋ ጥረት ውስጥሀሳቡን ይቀይራል። በዚህም ገፀባህርይ እንደ ሸንጎ አምስት የመገፋት ስሜት፤ የአስተዳደግ ጠባሳ ፍትህን በመፈለግ ሞራል ላይ ያሳትፈዋል

**ኀ. ሸንጎ አስራ *ሁለት*(የማስታወቂያ ባለሙያ)፡-** የዚህ ገፀባህርይ ሞራል ደግሞ በስራው ተፅዕኖ ላይ የወደቀ ነው። በማስታወቂያ ስራው በጣም ከመኩራቱ የተነሳ የሰዎችን ስብዕና የሚለካው እና ነገሮችን የሚመለከተው ከስራው አንፃር እንጂ በሰዎች ባህሪ ጠልቆ በመግባት አይደለም። እንዲሁም ለስራው ትኩረት ማድረጉ ለፍትህዊነት ቸላ ባይ እንዲሆን አድርጎታል።

*"**አስራ ሁለት፡** " ምን እንደማስብ ታውቃላችሁ ? ቢሮ ምን እየተካሄደ እንደሆነ ፡፡በማስታዊቀያ ኢንደስትሪ ውስጥ ለተሰማራ ሰው በዚህ ሰዐት እዚህ መገኘት ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ ? እውነቴን ነው ምላችሁ ፡፡ በስድስት ቀን ውስጥ ስራዩ በሙሉ ገደል ሊገባ ይችላል ፡፡ ምን ስራዩ ብቻ ጠቅላላ ደንበኞቼም ጥለውኝ ነው የሚሄዱት ...እደዚህ አይነቱን ስራ አይመቻቸውም (ኮቱን እያወለቀ መስቀያው እና መቀመጫቸው ለይ ማንጠልጠል ይጀምራሉ፡፡)"(ገፅ 9)*

*በዚህም ላይ ደግሞ ወላዋይ የሆነ ጥልቀት የሌለው ወይም ተጨባጭ የሞራል ውሳኔ ካለመወሰኑ የተነሳ ምርጫው ሁለት ጊዜ ከቀየረ በኋላ ነው የወጣቱን ጥፋተኛ አለመሆን ያመነው።*

## 3.3.2 ተውኔቱ የተለያዩ ሞራላዊ ዕሳቤዎችን ያነሳል?

በተውኔቱ የአንድ ወጣት የፍትህ እጣፈንታ አስራ ሁለት የሸንጎ አባላት እየተወያዩ እየተከራከሩ እርስ በእርስ በሚያጋጥማቸው የሞራል ሁኔታ ላይ ያተኮረ ተውኔት ነው። ተውኔቱ የፍትህ፤ ጭፍን ጥላቻ፤ ታማኝነት፤ ሞራላዊ ሀላፊነትን ይዳስሳል። ይህም የግለሰብ አድሏዊነት እና የሞራል ምርጫዎች እውነትን በመፈለግ ላይ እንዴህ ተፅዕኖ እንደሚፈጥሩ አጉልቶ ያሳያል። በዚህ ተውኔት የተንፀባረቁ ሞራላዊ እሳቤዎች እነዚህን ይመስላሉ፡-

## *ሀ.* ሞራላዊ አንፃራዊነት

በተውኔቱ ውስጥ የሸንጎ አባላቱ በአሳማኝ የክርክር ሂደት ሳይሆን አንፃራዊ በሆነ የግል እምነት፤ የአኗኗርዘይቤ፤ ማንነት እና አስተሳሰብ በመመስረት ተከሳሹ ላይ በመፍረድ የሞራላዊ አንፃራዊነትን ያሳያሉ። ደራሲውም ሸንጎ ስምንት(አርክቴክቱ) ገፀ ባህሪ በመጠቀም ይህንን አንፃራዊነት በመተቸት ፍትህ ከወገንተኝነት ይልቅ በእውነት ላይ መመስረት እንዳለበት ይገልፃል።

*"**ስምንት** እንድናወራበት ፤ ከመወሰናችን በፊት በጉዳዩ ለይ እናውራበት ነው ኢያልኩ ያለውት ፡፡ይሄ ልጅ እኮ ይህችን አስራ ምናምነ አመት እንኳን ተረጋግቶ መኖር የቻለ ልጅ አደለም፣ እናቱን በዘጠኝ አመት ያጣ*

*ልጅ ፣ መጠን ከፍ ያለ እና ስር የሰደደ  ችግር  ያለበት ሰፈር ውስጥ ያደገ ቁጡ ተናዳጅ ልጅ፣ ::እንደዚህ አይነት ችግር የበዛት  ውስጥ ያደጉ  ልጆችን የምናይበት መንገድ እኮ ትክክል አደለም ::፣ህይወት  ማቆየት በራሱ ከባድ ነው፣ ከዛ ማህበረሰ ውጭ  ያሉ ሰዎች የሚሠጣቸው  የተሳሳተ ግምት ደግሞ ነገሩን ያብሰዋል:: ኑሮው እና የመጣበት ሰፈርን መሰረት  አድርጎ  ወንጀለኛ ነው ብሎ መደምደም አግባባ ያለው አይመስለኝም"( ገፅ 13 )*

## ለ. የበጎነት ሞራል (የባህሪ እና የሞራል ታማኝነት)

በዚህ ተውኔት ፍትህዊነትን፤ ታማኝነትን፤ ድፍረትን፤ እና ቁርጠኝነትን የመሳሰሉ የሞራል ባህሪያትን ሸንጎ ስምንት(አርክቴክቱ) ገፀባህሪ ከታሪኩ ጋር ተላብሶ ይገኛል። እንዲሁም ደግሞ የሸንጎ አስር(ዘረኛው) ዘረኝነትን፤ የሸንጎ ሶስትን የግል ጭፍን ጥላቻን በማነፃፀር ግላዊ ባህሪ እንዴት በሞራላዊ ውሳኔ ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ያሳያል።

*"**ሰባት**፣አንድ ነገር ልንገርህ ይሄ ልጅ ወንጀሉን በትክክል ፈፅሟል :: መቶ አመት ብታወራኝ   ይህንን   አቋሜን ልታስቀይረኝ አትችልም*

***ስምንት**፣ እኔም የአንተን አዕምሮ መቀየር አልፈልግም*

***ሶስት**፣ ቆይ ቆይ ምንድን ነወ እያልክ ያለህው? ምንድን ነው የፈለከው?*

***ስምንት** እንድናወራበት ፤ ከመወሰናችን በፊት በጉዳዩ ለይ እናውራበት ነው እያልኩ ያለውት ::ይሄ ልጅ እኮ ይህችን አስራ ምናምነ አመት እንኳን ተረጋግቶ መኖር የቻለ ልጅ  አደለም፣ እናቱን በዘጠኝ አመት ያጣ ልጅ ፣ መጠን ከፍ ያለ እና ስር የሰደደ  ችግር  ያለበት ሰፈር ውስጥ ያደገ ቁጡ ተናዳጅ ልጅ፣ ::እንደዚህ አይነት ችግር የበዛት  ውስጥ ያደጉ  ልጆችን የምናይበት መንገድ እኮ ትክክል አደለም ::፣ህይወት ማቆየት በራሱ ከባድ ነው፣ ከዛ ማህበረሰ ውጭ  ያሉ ሰዎች የሚሠጣቸው  የተሳሳተ ግምት  ደግሞ ነገሩን ያብሰዋል:: ኑሮው እና የመጣበት ሰፈርን መሰረት  አድርጎ  ወንጀለኛ ነው ብሎ መደምደም አግባባ ያለው አይመስለኝም"(ገፅ 13)*

ሸንጎ ስምንት ገፀ ባህሪ ከተለያዩ ገፀባህርያት የውጭ ግፊት ተፅዕኖ ሲያሳድሩበት የበጎነትን እና ፍትህዊነትን ግዴታውን ስለሚወጣ ይሄን የሞራል እሳቤ ይወክላል። በተውኔቱም ከብዙሀኑ ጋር አብሮ በስሜት መነዳት ሳይሆን እንደ ሀላፊነት ሞራላዊ ግዴታን በመወጣት ማስረጃዎችን መርምሮ እውነትን ማግኘት እንደሚቻል በአግባቡ ተገልጿል።

## *ሐ. ነፃ ፍቃድ*

ግለሰቦች የራሳቸውን ሞራላዊ ፍች ይፈጥራሉ ወይም ነፃ ፍቃድ አላቸው። ነገር ግን ይህ ነፃ ፍቃድ በዚህ ተውኔት ውስጥ በተለያዩ የሸንጎ አባላት የእርስ በእርስ የአቻ ግፊትና የኋላ ታሪክ ተፅዕኖ ውስጥ ከሞራላዊ ሀላፊነት ያፈነገጠ ውሳኔ ይታያል። ለምሳሌ ሸንጎ አምስት(ወጣቱ) በሸንጎ አስር የዘረኝነት ተፅዕኖ ውሳኔውን ይቀይራል። ሸንጎ ሶስት በአለፈው የህይወት ታሪኩ ጠባሳ ተፅዕኖ ውስጥ ይወድቃል። በአጠቃላይ ተውኔቱ የግለሰቦች ነፃ ፍቃድ ከሞራላዊ ሀላፊነት ጋር ለምርጫዎቻቸው ተጠያቂነት መውሰድ እንደሚገባ ያስተላልፋል።የሰው ልጅም በተፈጥራዊ ማንነቱ በማህበራዊ አኗኗሩ ላይ ምን ያክል ጫና እንደሚፈጥር ደራሲው የገለፀበት መንገድ የሚደነቅ ነው።በመቀጠል ደግሞ በአስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት ከሞራላዊ ሂስ አንፃ ደካማ ጎኖች ተተንትነዋል፦

## 3.3.3 የስርዓት ኢፍትህዊነት

ተውኔቱ በስፋት የሚያነሳው በፍትህዊ ስርዓት ውስጥ ባሉት ሰፊ ጉድለቶች ሳይሆን በግለሰቦች ወገንተኝነት ላይ ነው። የዘርና የመደብ ጥላቻን ቢተችም እንደ ህግጋትና ደንቦች ያሉትን ጉዳዬች እኩል አለማቅረብ ወይም በወንጀልና በቅጣት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ማህበራዊ፤ ፖለቲካዊ፤ የመሳሰሉ ጥልቅ ስርዓታዊ ጉዳዬችን አለመመልከቱ ከስርዓታዊ የሞራል ጥያቄዎች አንፃር ደካማ ጎኑ ያደርገዋል።

## 3.3.4 የፍትህና የምህረት ክርክር

ሌላኛው የተውኔቱ ክፍል ደግሞ የክርክሮች ሞራላዊ ሂደት ነው። በተውኔቱ ከመጀመሪያ ጀምሮ (በሸንጎ ስምንት) በተከሳሹ ላይ የርህራሄ ስሜት ለፍትሀዊ ክርክር እስከመጨረሻው የተውኔቱ ክፍል ሲንፀባረቅ ይታያል። ይህም ምክንያታዊነትን ከልክ በአለፈ የርህራሄ ተፅእኖ ውስጥ ማድረግ ሌላኛ የሞራላዊ ፍትህ ስጋት ይሆናል።

*"**ስምንት** እንድናወራበት ፤ ከመወሰናችን በፊት በጉዳዩ ለይ እናውራበት ነው እያልኩ ያለውት ፡፡ይሄ ልጅ እኮ ይህችን አስራ ምናምነ አመት እንኳን ተረጋግቶ መኖር የቻለ ልጅ አደለም፣ እናቱን በዘጠኝ አመት ያጣ ልጅ ፣ መጠን ከፍ ያለ እና ስር የሰደደ ችግር ያለበት ሰፈር ውስጥ ያደገ ቁጡ ተናዳጅ ልጅ፣ ፡፡እንደዚህ አይነት ችግር የበዛት ውስጥ ያደጉ ልጆችን የምናይበት መንገድ እኮ ትክክል አደለም"(ገፅ 13)*

## *3.3.5 የግለሰብ ሞራላዊ ጀግንነት*

ይህ ተውኔት ሸንጎ ስምንትን(አርኪቴክቱ) ገፀባህርይ የአስራ አንዱን የሸንጎ አባላት ሀሳብ የሚያስቀይር የሞራላዊ ጀግና አድርግ አቅርቧል። ደራሲው በተውኔቱ እንደ ገፀባህርይ የራሱን የአሳሳል ጥበብ ቢጠቀምም የጋራ አስተሳሰቦች እና ስርዓታዊ ጉዳዮች ብዙ ጊዜ የግለሰባዊ በጎነት የሚያሸንፉበትን የገሀዱን አለም ሞራላዊ ውሳኔዎችን ቀለል አድርጎ ማየቱ እና በሸንጎ ስምንት ገፀባህርይ ከመጠን በላይ የሆን የሞራላዊ ጀግንነት ማላበስ ከእውነታዊው አለም ጋር ተዓማኒነትቱ ያጠራጥራል። ይሄም በግለሰብ ሞራላዊ ጀግንነት ላይ ከመጠን በላይ መተማመን የተውኔቱ ደካማ ጎን ያደርገዋል።

## 3.4 ተውኔቱ ከሞራላዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ለማህበረሰቡ ያለው ጠቀሜታ

አስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት ከሞራላዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ትልቅ አስተዋፅኦ ይዞ የመጣ ተውኔት ነው። የሰውን ልጅ ውስብስብ የሆነ ሞራላዊ አመለካከቶችን ስርዓታዊ ፍርድ ውስጥ በማንፀባረቅ እውንነትንና ፍትህን ለማግኘት የሚደረግን ትግል ተውኔቱ ያሳየናል። ይህ ተውኔት በውስጡ ከያዘው ሞራላዊ ሀሳብ አንፃር ለማህበረሰቡ ያለው ጠቀሜታ እንደቀላል የሚታይ አይደለም። የፍርድ ስርዓቶች በተለያዩ አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች እውነት ተደብቆ ፍትሀዊ ያልሆን ፍትህ በማህበረሰቡ ላይ ሊከሰት ይችላል። ታዲያ ይህ ተውኔት በፍርድ ስርዓት ላይ ለሚገኙ የህግ ባለሙያዎች ብልሹ ሞራላቸው በሚያካሂዱት ፍርድ ላይ ስህተት ውስጥ እንዳይገቡ ጥልቅ የሆኑ መልዕክቶች ይዟል። ማህበረሰቡም ፍትሀዊ የሆነ የህግ ስርዓት እንዲያገኝ ትልቅq1 ሚና ይጫዎታል። በተጨማሪም እንደ ግለሰብ ይህንን ተውኔት የተመለከተ ሰው በራሱ ሞራላዊ ውሳኔ ላይ ወይም አመለካከት ላይ ጥያቄ እንዲያነሳ ያደርገዋል።

# ምዕራፍ አራት

## 4. ማጠቃለያ

አስሩ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት በ2017 ዓ.ም በሀገራችን ለዕይታ ቢበቃም ለአለፉት ሰባት አስርት አመታት በተለያዩ ሀገራት እንደ አተረጓጎም ስርአቶች ወደ ራሳቸው ባህልና ቋንቋ መሰረት ተውኔቱ ተሰርቷል። ምክንያቱ ደግሞ ተውኔቱ በውስጡ የያዘው ፅንሰ ሀሳብ መላው የሰውን ልጅ የሚያያዝ በመሆኑ ነው። ወደ ሀገራችንም ይህ ተውኔት ሲመጣ ይህኑን ጭብጡን ሳይለቅና በጥሩ የአተረጓጎም ዘዴ መሆኑ ይበል የሚያሰኝ ነው። አጥኝውም ይህንን ተውኔት ከሞራላዊና ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር መተንተኑ አንዱ እንደ ሰው ልጅ የሚያሳስቡ ሁለት ፅንሰ ሀሳቦችን ተውኔቱ በውስጡ ስለሚያሽከረክር ነው። አስራ ሁለቱ እንግዶች ተውኔት ውስጥ የአስራ ሁለት የሸንጎ አባላት ሞራላዊ እሳቤ ልዩነት የሰውን ልጅ ውስብስብነቱን በመግለፅ ይህ ሞራሉ በውሳኔውና በእያንዳንዱ እርምጃው ላይ ያለውን ተፅእኖ እና ጥቃቅን የመሰሉ ነገር ግን ግዙፍ ሞራላዊ አመለካከቶች ያላቸውን ዋጋ በግሩም ሁኔታ የሚገልፅ ተውኔት ነው። የገፀባህሪያቱ ሙብዛት የሞራላዊ ፅንሰ ሀሳቦች በተለያዩ የሀሳብ ሰዎች፤ ፈላስፋዎች የተፀነሱ ንድፈ ሀሳቦችን ወክለው ይገኛሉ። እንዲሁም ደግሞ አጥኝው ሌላኛው ጥናቱን ያደረገበት ፅንሰ ሀሳብ የዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ ነው። ይህም ሌላኛው እንደ አለም የሚያሳስብና ችላ የማይባል ጉዳይ ነው። ዘረኝነት በተለያዩ ጉዳዬች ላይ ስር እንደመስደዱ ተውኔቱ ይዞት ከተነሳው የፍርድ ስርዓት እና ከተፃፈበት ጊዜ አንስቶ እየቀጠለ ያለ ጉዳይ ነው። ለዚህም ነው ተውኔቱ ዘላቂነትን የያዘ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ተውኔት የሆነው። አጥኝውም ይህንን ተውኔት ከሁለቱ የሂስ ፅንሰ ሀሳቦች ላይ በመመርኮዝ ጥናታዊ ፅሁፉን ሲያቀርብ ደካማ እና ጠንካራ ጎኖቹን ከነመፍትሄ ሀሳቦቻቸው አቅርቧል።

## 4.1 የጥናቱ ግኝት እና የመፍትሄ ሀሳብ

በአስራ ሁለቱ እንግዶይ ተውኔት በሁለቱ የሂስ ፅንሰ ሀሳቦች ማለትም ከሞራላዊና ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ተተንትኗል። ተውኔቱ ከፅንሰ ሀሳቦቹ አንፃር የሚበረታቱ ጥሩ ጎኖች ቢኖሩትም ደካማ ጎኖቹም ይዞ ይገኛል።

ከዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር የነበሩ ደካማ ጎኖች የመፍትሄ ሀሳቦቻቸው እንደሚከተሉት ተገልፀዋል፡-

***ሀ. የስርዓቶች ወይም ተቋማዊ የዘረኝነት ምርመራ፡-*** በጥናቱ ምዕራፍ ሶስት እንደተገለፀው ተውኔቱ እንደ ዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር አንደኛው ድክመት የስርዓቶች ወይም ተቋማዊ የዘረኝነት ምርመራ በተውኔቱ አለመኖሩ ነው። ይህም ከፅንሰ ሀሳቡ ዋነኛ መነሻ አንፃር ደካማ ጎኑ ያደርገዋል። ለዚህም እንደመፍትህሄ ሀሳብ የተወሰደው ደግሞ ዘረኝነት ይበልጥ ከሰው ልጆች አመለካከት በላይ ይበልጥ ጉዳቱ ተቋማዊ አገልግሎቶች ላይ መሆኑ ወደፊት ለሚመጡ ፀሀፊያን ይበልጥ በጉዳዩ ዙሪያ በስርዓቶችና በተቋማት ላይ የሚያንፀባርቁ የዘረኝነት ሀሳቦች ላይ ትኩረት ማድረግ ነው።

**ለ. የተለያዩ ውክልናዎች፡-** በተውኔቱ ይበልጥ እንደ ዘረኝነት አገላለፅ የተለያዩ ገፀባሕርያት የተለያዩ የዘር ውክልናዎችን ይዘው አለመቀረፃቸው አንዱ ድክመት ነው። ምክንያቱም እንደ ገፀባህርያት ብዛታቸውና እንደ የሰው ልጅ የብሄርና የዘር ብዛት አንፃር ገፀባሕርያቱ የተለያዩ የዘር ውክልናዎችን ይዘው መቅረብ ነበረባቸው። ለዚህም እንደ መፍትሄ ሀሳብ ምን አልባት ገሀዳዊ የዘር ወክልናዎችን መስጠት ከተመልካች ዘንድ ቅሬታ ሊያቀርብ ስለሚችል በተለየ ውክልና ዘዴ ደራሲ በምዕናቡ አለም የተለያዩ ውክልናዎችን መፍጠር ነው።

**ሐ. የተከሳሹ አመለካከት፡-** በተውኔቱ ሌላኛው ደካማ ጎን ደግሞ የታሪኩ መነሻ የሆነው ተከሳሹ ገፀባህሪ ግልፅ ያልሆነ የማንነትና የአመለካከት አሳሳል ችግር ነው። እንደ ዘር ሂሳዊ ፅንሰ ሀሳብ የታፈኑ ድምፆች በገፀባህሪያት ተወክለው ሲቀርቡ ግልፅ የሆነ አመለካከቶችን እንዲኖርባቸው ቢገለፅም ተውኔቱ ግን የገፀባህሪውን አመለካከት አልገለፀም። ለዚህም መፍትሄ ሀሳብ የተገፉ አካላትን በተውኔቱ አለም በገፀባህሪያት በመወከል መገፋታቸውን በደላቸውን ከራሳቸው አንደበት ተናግረው ለተመልካቹ ስሜታቸውን ማካፈል እንዲችሉ እንደ ደራሲ መፍቀድ ነው።

ከሞራላዊ ሂስ አንፃር የተውኔቱ ደካማ ጎኖችና መፍትሄዎቻቸው፡-

***ሀ. የስርዓት ኢ-ፍትሀዊነት፡-*** ተውኔቱ የሚያተኩረው የገፀባህሪያቱ ሞራላዊ እሳቤ በፍትህ ስርዓቱ ላይ ያለው ተፅዕኖ ላይ እንጅ የስርዓቱ ወይም የደንቡ ኢ-ፍትሀዊነት ላይ አለመሆኑ አንዱ ደካማ ጎኑ ያደርገዋል። ለዚህም የመፍትሄ ሀሳቡ በገፀባህሪያት ሞራላዊ አስተሳሰብ ላይ የስርዓቶችን ኢ-ፍትሀዊነት እንቅስቃሴ ማጉላት መቻል ላይ ነው። ይህም የተውኔቱን ይዘታዊ ጭብጥ ያጎላዋል እንጅ አያደበዝዘውም።

**ለ. የፍትህና የምህረት ክርክር፦** በተውኔቱ ከፍተኛ የሆነ ርህራሄ የሞላበት የምህረት ክርክር በአንድ ገፀባሕርይ ተነስቶ ከሌሎች ምክንያታዊነቶች በፊት ሲጋፈጥና ሲያሸንፍ ይታያል። ይህም ደግሞ ምክንያታዊ የሆኑ ክርክሮች ከሞራላዊ ፍትህ አንፃር ዋነኛና አስፈላጊ እንደመሆናቸው በተውኔቱ የርህራሄ ፍርዳዊ እንቅስቃሴ ተጀምሮ ምክንያታዊነት መቀጠሉ እንደ ደካማ ጎን ይታያል። ለዚህ የመፍትሄ ሀሳቡ ደግሞ የሞራላዊ ይዘት ያላቸው የክርክር ሀሳቦች፤ ምክንያታዊና ማስረጃዊ የውይይት ሀሳቦችን በማራመድ ውስጥ ሰዋዊ የሆነ ርህራሄ ማቅረብ ነው።

**ሐ. የግለሰብ ሞራላዊ ጀግንነት፦** በምዕራፍ ሶስት እንደተገለፀው የሸንጎ ስምንት ከመጠን ያለፈ የበጎነትና የምክንያታዊነት ክርክር እንደ ተውኔትና እንደ ነባራዊው አለም አሳማኝ ያልሆነ የግለሰብ ሞራላዊ ጀግንነት አቀራረፅ ነው። ለዚህም ገፀባህርይውን እንደ ሰውኛ ባህሪያት መጠነኛ የጥርጣሬ መንፈስ እና ከራስ ጋር የሁለት ተቃራኒ ሀሳቦች ግጭት ማሳየት እንዲቻል አድርጎ መሳል ይቻላል።

# ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

1st. The critical race theory movement is a diverse group of scholars who seek to study and transform the relationship between race and power. This movement addresses many of the issues traditionally addressed by civil rights and race studies, but it also examines these issues in the context of economics, history, contextual conditions, and the pressures of group and individual interests (Richard Delgado and Jane Stefencic:1992.1)

**2nd.** The goal of critical race theory is to first understand how white supremacy and the inferiority complex of people of color in America were created and maintained, and to examine the relationship between that social structure and the ideas of the system of rule. (Thomas.Peller.Gotanda; 1983. 2)

**3rd**. Racism is a common practice among people of color.

The judicial and political systems in America are inherently racist.

The idea that laws are neutral leads to discrimination.

Race is a social construct.

White intellectuals only do something if it benefits them. (www.studysmarter.co.uk)

**4th**. Where, in what ways, and for what purposes is racism manifested, shaped, and reflected in the dominant body?

In what ways does the dominant body reflect its views on race?

How do scholars or artists convey that racism is a threat to all segments of society?

Are the experiences of victims of racism accurately reflected?

Who is the victim or oppressed by racism in works of art?

How are characters who represent the real world depicted in the works of art in terms of racism? (www. Scholarship.law.nd.edu.com)

**5th.** A critic who does moral criticism is concerned with what is said and what is presented in the work. He is not concerned with how it was presented. In this type of criticism, the strength or weakness of literary works is judged in terms of the morality of the time that the work reflects. He assesses how much humanity is reflected in the work according to the known moral principles of the time. He examines how much the work reflects the moral principles of that time and whether it contributes to a cause that is beneficial to society based on moral principles. The criticism will also revolve around this. What can a reader learn about life from creative works? How much good morals can the reader inherit from the story? He studies these things. In general, the main purpose of this criticism is to examine how much the literary work reflects moral values. Although criticism is a primary form of criticism, it has faced many criticisms. Among them is the claim that its focus on content rather than aesthetics or creativity has undermined the aesthetic value of literature: ( http//: eopcw.com)

**6th.** Moral Content and Message - What moral values and messages does the work of art convey? Are the ideas and actions contained in it morally correct or not? Morality of Characters - How are the characters in the work of art morally expressed? What impact might their behaviors and actions have on viewers or readers?Impact of the Work of Art - What impact might the work of art have on society? Can it promote moral corruption or wrong views?Responsibility of the Artist - Does the artist have a responsibility to create works of art that have moral content? How should the balance between artistic freedom and moral values be? What moral lesson does the author present through the characters in the work, through plot or theme? How do they represent moral principles? Does the artwork convey a moral lesson or philosophical idea? (http//:www.prezi.com)

## ዋቢ መፅሀፍት

አለም እሸቱ። መሰረታዊ የዘገባ አፃፃፍ ዘዴ። አዲስ አበባ። ብረሀን እና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።1994 ዓ.ም

ወንደሰን ሽመልስ። የሰብዓዊነት መንጠፍ ኪናዊ ፈርጆችና ረቦች በየሕሊና ባርነት ልቦለድ ውስጥ። ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማረኛ ቋንቋ ስነፅሁፍና ፎክለር ት/ት ክፍል ባችለር ድግሪ ሟሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ። 2010 ዓ.ም

የሻው ተሰማ። የተውኔት አፅናፍ መነፅር፤ አዲስ አበባ። ብርሀንና ሰላም ማተምያ ቤት።1998 ዓ.ም

ፊንታሁን እንግዳ።የተውኔት ድርሠት አፃፃፌ ዘዴ። አዲስ አበባ፣ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣1999 ዓ.ም

ደበበ ሰይፉ። የቴአትር ጥበብ ከፅሀፈ ተውኔቱ አንፃር። አዲስ አበባ። ንግድ ማተሚያ ቤት።1973 ዓ.ም

ፊንታሁን እንግዳ።የተውኔት ድርሠት አፃፃፌ ዘዴ። አዲስ አበባ፣ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣1999 ዓ.ም

Richard Delgado & Jean Stefancic:Critical Race Theory: The Cutting Edge.eds., 2d ed. 2000

Tomas Kendall. Kimberlé Crenshaw, Neil Gotanda,Gary Peller & Critical Race Theory: The Key Writings That Formed the Movement.eds., 1995

www. Scholarship.law.nd.edu.com

www.studysmarter.co.uk

http//: Bentonenglish.com

http//: eopcw.com

https://manuals.plus

http//:www.prezi.com